17. ዘሩ በቀለ

"ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው። . . .
እግዚአብሔር ያሳድግ ነበረ።"


(ሉቃስ 8፡11 1ቆሮ 3፡16)



አቶ ብሩ ዳባለ



አቶ ዋንዳሮ ደባሮ



አቶ ሰብሮ ወሰሮና አቶ ሽጉጤ ዳዳ
በጉልምስና ጊዜያቸው
ምንጭ ፡ Cords of Love

ሚስዮናውያኑ ለስምሪት ከአዲስ አበባ ከወጡበት ከመጋቢት ወር1920 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ ወር 1921 ዓ.ም. ድረስ በሁሉም ጣቢያዎች (ወላይታ፥ሲዳማ፥ከምባታና ሃዲያ እና ማረቆ) የሚኖሩት አገልጋዮች ተደላድለው ስላልተቀመጡ ይህ ነው የሚባል የወንጌል ስርጭት ሥራዬ ብለው አላከናወኑም ነበር፤ ሁኔታውም አይፈቅድላቸውም ነበር። ከአራቱ ጣቢያዎች ግን ወላይታ ለየት ያለ ዕድል ነበረው፤ ዕድሉን ያሰፋው ከአገሪቱ ዋና ከተማ ከአዲስ አበባ ከተማ ይልቅ ለኤስ አይ ኤም ሚስዮን እንደ ማእከል ሆኖ ማገልገሉ ነው። ከዚህም የተነሣ በወላይታ የሚስዮን

ጣቢያ በርካታ ሚስዮናዊያን ከመስፈራቸውም በተጨማሪ ብዙ የግንባታ ፕሮጀክቶችም ተከናውነው ነበር።

እንደ ሥራው ብዛት የአገሬው ተወላጆችም በተለያዩ የጉልበት ሥራዎች ተቀጣሪና ተጠቃሚም ሆነው ነበር። በየሚሲዮን ጣቢያዎቹ የአገሬው ተወላጆች ሥራ ማግኘታቸውና ከፈረንጆቹ ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠራቸው በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ የአስተሳሰብ ለውጥ አስከትሎ ነበር።

በሰሜንና በማእከላዊው የአገሪቱ ግዛቶች ከአድዋ ጦርነት በኋላ ስር ሰዶ የቆየው ፀረ ጣሊያን አልፎም ፀረ ፈረንጅ አመለካከት በሕዝቦች መካከል ግዙፍ የግንኙነት ገደል የመፍጠሩን ያህል በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ደግሞ የደራ ገበያ የነበረው "የባሪያ ፍንገላ" ወይም የባሪያ ንግድ በሕግ የተከለከለ ቢሆንም የሕጉ ተግባራዊነት እጅግ የዘገዩ ነበር። በዚህ የተነሣ የደቡብና የጠረፉ አካባቢዎች እንግዳ ሰው ሲያዩ ወዲያው በአእምሮአቸው የሚከሰተው ባሪያ ፍንገላ ነበር።

ቀዳሚዎቹ ወንጌላውያን ከአገሬው ሰዎች ጋር በተገናኙ መጠን በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ንጹሕነታቸውን አስመሰከሩ።

መነጽር የሚጠቀሙቱን ደግሞ "አራት ዓይና" ናቸው÷ "ሰውን ይበላሉ "የሚባለውን ሐሜት ስለሰሙ ፈረንጆች ከአደጉበት ባህል አልፈው ጓዳቸውን ሁሉ ክፍት አደረጉላቸው። ከአገሬው ልጆች መካከል ቀደም ብለው እንደፈሩት የተሸጠም÷ የተገዛም÷ የታረደም የተበላም እንደሌለ ሲረዱ ግን ቀስ በቀስ ሚስዮናዊያኑን ተላመዷቸው። ሌላውና በአርአያነቱ የሚጠቀሰው መልካም ርምጃ ሚስዮናውያኑ በየደረሱበት አካባቢ ሰፍረው ኑሮ ሲጀምሩ የራሳቸውን ትንንሽ ደሴቶች አለመፍጠራቸው ነበር። ከጥቂት ማስተካከል በስተቀር የአገሬውን ጎጆ ቤቶች ዓይነት ነበር የሠሩት። በሠሩት ጎጆ ቤት ውስጥ ምድጃ ላይ እሳት አንድደው ከሚንቀለቀለው እሳት ዙሪያ ከበው ቡና እየጠጡ÷ ቆሎ እየቆረጠሙ ከአገሬው ሰው ጋር ያወራሉ፤ ወይንም ደግሞ በጠራ ጨረቃ ከቤታቸው በር ላይ ተቀምጠው ወይንም ቀን በጠራራ ፀሐይ ከዋርካ ዛፍ ጥላ ስር እየተዝናኑ ተወላጁ የልቡን ስሜት እንዲያወራ መንገድ ይከፍቱለታል። ከአስጨናቂ ገጠሮቹና ከባሪያ ፈንጋዮቹ ይልቅ እኒህ ሰዎች በሕዝቡ ዘንድ መታመንን አገኙ። ወንጌልን ከመመስከራቸው በፊት አስቀድመው የዘሩት እና ያጨዱትም ፍቅርን ነበር።

የሁለተኛው ዓመት ቆይታቸው (1923 ዓ.ም.) ከመገባደዱ በፊት ከየጣቢያዎቹ የማይሞተው የወንጌል ዘር በአስገራሚ ሁኔታ የመብቀሉ ዜና በየአቅጣጫው ተሰማ። ቀዳሚውን ድርሻ የወሰደው ወላይታ ነበር። ኢቲ ብሩ ዱባለ በወጣትነታቸው በስዊዲን ሚሲዮን የሰሙትን ቃል አጸኑ፤[28] አቶ ዋንዳሮ፥አቶ ደስታ፥አቶ ጎዳና፥አቶ ግንጃ፥አቶ አሬቦ አቶ ኮና ኩባ፥አቶ ወልዴ፥አቶ ጮራሞ እና ባለቤታቸው ፓካሬ በኋላም የአቶ ደስታ ባለቤት ወይዘሮ ዲያጣ በወንጌል ኃይል ሕይወታቸው ተማረከ።

በሲዳማም እንዲሁ፤ አቶ ገነሜ ሑንዴ የተባሉ የቤተሰብ ኃላፊ የመጀመሪያው የሲዳማ ክርስቲያን አማኝ ሆኑ፤ቀጥሎ አቶ ሆሼ የተባለ ጎልማሳ ተከተለ፤ አቶ ጋኖቤ አቶ አርቲሳ፥ አቶ ቱቴሳ፥ አቶ ባለሞ በአንድ ሰሞን ወደ ክርስትና እምነት ፈታቸውን አዞሩ። በከምባታና ሃዲያ (በላምቡዳ ጣቢያ) ፈረንጆች የ1923 ዓ.ም የገና በዓላቸውን ለማክበር አንድ ሳምንት ያህል ሲቀራቸው በመጀመሪያው አማኝ ልብ ውስጥ የክርስቶስ እምነት ተወለደ። በታህሣሥ 18 ቀን 1923 ዓ.ም የወንጌል መልእክተኛው በታላቅ የደስታ ስሜት የተዋጠ የምሥራች ደብዳቤ ለቤተሰቦቻቸው እንዲህ ሲሉ ጻፉ፤

> . . . ከእንዲህ ያለ መልካም ዜና የበለጠ ሌላ ነገር ልልከላችሁ የምችል አይመስለኝም። ከሁሉ የተሻለው የአካባቢው ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲቀበል ምክንያት ሆኖለሁ! ሰብሮ የልደት በዓል ሊከበር ትንሽ ቀናት ሲቀረው በመንፈስ ቅዱስ እንደገና ተወልዶ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆኗል። ይህ ነው የገና በዓልን አይቼ በማላውቀው ደስታ እንዳሳልፍ ምክንያት የሆነኝ።[29]

በረኸሙ ደብዳቤ ማጠቃለያ ላይ፤". . .ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገረ በእርግጥ ገብቶታል፤...ይህንን ሲነግረኝ በዓይኑ ላይ እንባ ተንቆርዝዞ ነበር . . .። ከወገኑ የመጀመሪያው ፍሬ እሱ ነው።"[30]


አቶ ሰብሮ ካመኑ ከሁለት ቀን በኋላ ደግሞ አቶ ሽጉጤ ዳዳ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው መቀበላቸውን በይፋ መሰከሩ። ከእነዚህ ከሁለቱ ሌላ አቶ ቱለሮ፥ አቶ ባቦ፥ አቶ ሻፈሶ ባመኑት ላይ ተጨመሩ። አቶ ሙሉነህ ቀዳሚ አማኞችን ከኋላ በሩቅ እየተከተሉ ያዘግሙ ነበር።

በአራተኛው የሚሲዮን ጣቢያ በማረቆ እንማን መቼ ወደ ክርስትና እምነት እንደመጡ የተቀመጠ የታሪክ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም። ነገር ግን በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ ስማቸው የቤተሰብ ያህል ቅርብ የሆነው አቶ ደምበል ሚስዮኑ ማረቆ ከመግባቱ አስር አመት ቀደም ብሎ ወንጌልን መቀበላቸው ታውቋል። አቶ ደምበል ሕይወታቸው የተለወጠው በዚያን ዘመን ብርቅ የነበረውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በማላቸው ሲያነቡ መንፈስ ቅዱስ በተለየ አኳኋን የደኅንነትን ምስጢር ስለገለጠላቸው ነበር። እኒህ ሰው ለጌታ ሥራ የተመቹና የማረቆ ሚስዮናውያንን ሥራ በብዙ ያገዙ ሰው ነበሩ። በጣሊያን ወረራ ጊዜም ሚስዮናውያኑን በቤታቸው ውስጥ በመሸሸግ እና አዲስ አበባ ድረስ በመሸኘት ሕይወታቸውን ታድገዋል።

መጀመሪያ በተቋቋሙት የመንጌል ሰበካ ጣቢያዎች በቀዳሚነት አምነው ከአራት ሺህ አጥቢያዎች በላይ ላቀፈችው የዛሬዋ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ማህፀን የሆኑት እኒህ ከላይ የዘረዘርናቸው ናቸው ፡ የቤተክርስቲያኒቷን ታሪክ በመረመርን ቁጥር ስለ እነዚህ ሰዎች በተጓዳኝ የምንሰማው ታሪክ የእግዚአብሔርን መልካምነት በተራው ሰው ሕይወት ውስጥ የታየውን የመዓዛ ሽታ እንድናደንቅ እንገደዳለን።

አስቀድመው ባመኑት ላይ ስለተጨመሩት አዳዲስ ሰዎች ብዛት የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ግምት አላቸው። ነገር ግን በወላይታ፥ በሲዳማ እና በከምባታና ሃዲያ (ላምቡዳ) የወንጌል ሥራው ከተጀመረ ሁለት አመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ 30 ያህል አማኞች እንደነበሩ ታውቋል። የሚስዮናውያኑ ቁጥር ደግሞ በአዲስ አበባ ቢሮ ያሉትን ጨምሮ በወላይታ፥ በከምባታና ሃዲያ፥ በሲዳማ እና በማረቆ ተመድበው የሚያገለግሉት ቁጥር ሃያ ሁለት ደርሶ ነበር።

18. ድንበሩ ሰፋ



የኤስ· አይ· ኤም ጣቢያዎች የተቋቋሙባቸው አካባቢዎች (1926)

ምንጭ ፡ Born At mid night

በ1923 ዓ.ም አጋማሽ ላይ የጎፋ ጠቅላይ ገዢ ደጃዝማች መርድ ከዋና ከተማቸው ከቡልቂ ተነሥተው በድንገት ሶዶ ከተማ ዳርቻ ላይ በኦቶና በተቆረቆረው የሚስዮን ጣቢያ ደረሱ። የመጡበት ምክንያት በዝና የሰሙትን የሚስዮን ሥራ በዓይናቸው ለማየት ነበር። ሐኪም ቤቱን፥ ትምህርት ቤቱን፥ መኖሪያ ቤቶቹን ሁሉ ተዘዋውረው ጎበኙ። ከሁሉም ይልቅ በትምህርት ቤቱ ሥራ ተመሰጡ። ዶ/ር ላምቤ በሌሉበት ጊዜ በኃላፊነት የሚሠሩትን ሚ/ር ሮድን ጎፋ መጥተው ተመሳሳዩን ልማት እንዲያከናውኑ ጋበዙአቸው፤ ይህም ብቻ አይደለም የአንድ መቶ ብር ስጦታ ሰጥተዋቸው ወደ አዲስ አበባ አለፉ። አልተመለሱም፤ በሄዱበት በዚያው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። መርዷቸው መጣ።

ሰውዬው በቤተመንግሥት ውስጥ ባለክብር ስለነበሩ፤ ሹመታቸው ለሌላ ሰው ሳይተላለፍ ለልጃቸው ለደጃዝማች በየነ መርድ ተሰጠ። ደጃዝማች በየነ የልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት ናቸው። ደጃዝማች በየነ በአባታቸው ምትክ ወደ ተሠጣቸው ግዛት ሲመለሱ እግረመንገዳቸውን አቶና ጎራ ብለው የአባታቸውን የመጀመሪያ ጥያቄ ለሚስዮናውያኑ አጸኑ። በዚህም የወንጌል መልእክተኞችን ድንበር ወደ ደቡብ ያሰፋው አምስተኛው የሰበካ ጣቢያ በጎፋ ተከፈተ።

በጎፋ በአምስተኛው አዲስ ጣቢያ እንዲሠሩ የተመደቡት ሚ/ር ዋልተር አህማን ከቀዳሚዎቹ የወንጌል መልእክተኞች አንዱ ናቸው። ባለቤታቸው ማርሴላ ፖል ግን ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ዘግይተው ነው። መጥተውም ገና አንድ አመት ሳይሞላቸው ነበር ከአህማን ጋር የተጋቡት።

በመሠረቱ ሚስዮናውያን እርስ በርስ ከመጋባታቸው በፊት ቢያንስ አንድ ዓመት በተሰማሩበት አገር መቆየት እንዳለባቸው የሚያስገድድ ደንብ ወጥቶ ነበር። ቢሆንም በጎፋ የዋልተር አህማን አስፈላጊነት ከደንቡ መከበር ይልቅ ስለ በለጠ ሚ/ር ዳፍ እንዳሉት ደንቡን በመጠኑም ቢሆን ገድፎ የካቲት 11 ቀን 1923 ተጋቡ። በኢትዮጵያ ውስጥ ትዳራቸውን የመሠረቱ የመጀመሪያዎቹ አሜሪካውያን እነዚህ ሚስዮናውያን ናቸው።

ሁለቱ ሰዎች በተጋቡበት ዕለት ከሰዓት በኋላ ወደ ጎፋ ይዘውት የሚሄዱት ጓዝ ቀድሞ ከአዲስ አበባ ወጥቶ አደረ። የጫጉላ ጊዜያቸውን እንኳን በወቅቱ ከሁሉም በተሻለው ስፍራ በአዲስ አበባ ለማሳለፍ ልባቸው ሳይከጅል እነሱም ጓዛቸውን ተከትለው ወጡ፤ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ የበለጠ ደስታ የለምና።



ዋልተር አህማን
ምንጭ ፡ Cords of Love

ጉዞው ለሚ/ር አህማን አዲስ አልነበረም፤ ከአራት ቀናት በኋላ ማረቆ ደረሱ፤ በስምንተኛው ቀን ደግሞ ላምቡዳ ከዚያም ወላይታ ሶዶ። በወላይታ ሶዶ ሁለት ሳምንታት ያህል ከዓረፉ በኋላ በሚያዝያ 8 ቀን 1923 ዓ.ም. ወደ ጎፋ ጉዞ ጀመሩ። በዚህን ወቅት ሦስተኛ ባልደረባ ሚ/ር ሎሪ ዳቪሰን ተጨመሩላቸው። ዳገት ቁልቁለቱን ወጥተው ወርደው ታላቁን የማዜ ወንዝ በብዙ መከራና ትግል ከተሻገሩ በኋላ ሰፈር ባደረጉበት ቦታ እግዚአብሔር መልካም እንዳደረገላቸው የሚመሰክሩበትን ስጦታ የአካባቢው ሕዝብ አቀረበላቸው። በጎች፥ ፍየሎች፥ ዶሮዎች፥ እንቁላልና ሌላም ብዙ በረከት በአካባቢው ሹም በኩል ለመስተንግዶ ተሰጣቸው። የጎፋ አውራጃ የመንግሥት መቀመጫ እንደዛሬው ሳውላ ሳይሆን ቡልቂ በመሆኑ እንዲመጡ የተጋበዙት እዚያ ነበር። ጉዞአቸውን ወደፊት ቀጥለው ከሶዶ በተነሱ በ14ኛው ቀን ሚያዝያ 22 ቀን 1923 ዓ.ም .ሆቶ ቀበሌ ደርሰው አዳር አደረጉ። ሆቶ ቡልቂ ከተማ ለመድረስ ሦስት ወይም አራት ኪሎ .ሜትር ሲቀር የምትገኝ ተራራማ ቀበሌ ነች። በማግሥቱ ደጃዝማች በየነ መርድ ከጦር አበጋዞቻቸው ጋር ሆነው የክብር አቀባበል አደረጉላቸው። በወደዱት ቦታም ጣቢያ እንዲመሠርቱ ምርጫውን ለሚስዮናውያኑ ተውላቸው።

የደቡብን ድንበር እስከ ቡልቂ ያሰፋላቸው አምላክ ጊዜውን ጠብቆ ቀደም ብለው ባለሙለት በጂማ (ጅራን) ስድስተኛው የሰበካ ጣቢያ እንዲከፈት መንገዳቸውን አቀናላቸው፥ የሚስዮኑ ሁለተኛ ሰው ሚ/ር ሮድ የጂማውን ጣቢያ ከከፈቱ በኋላ በዚያው ዞረው የጎጀብንና የኦሞን ወንዝ

በመሻገር እነ ኦህማን ቡልቂ በገቡ በአስረኛው ቀን ጎፋ ደረሱ። በዚያን ጊዜ በቡልቂ አካባቢ የሰፈረው ሕዝብ ብዛት ከሃምሳ እስከ ስልሳ ሺህ ብቻ ነበር። ከወላይታ ወይም ከከምባታና ሃዲያ ሕዝብ ብዛት አንጻር ሲያዩት ትንሽ ቅሬታ ቢፈጥርባቸውም እግዚአብሔር ለአንድም ነፍስ እንኳን ቢሆን ግድ የሚለው አምላክ ነውና በሙሉ ትጋት ሥራቸውን ጀመሩ። የደጃዝማቹ ጥያቄ የሆነውን ትምህርት ቤት የማቋቋሙ ጉዳይ የማይቀር ቢሆንም ሕዝቡ አስቀድሞ ያገኘው አገልግሎት ሕክምና ነበር። ሚ/ር ኦህማን ወላይትኛ ቋንቋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የመግባባት ክፍተት አልተፈጠረም። እነ አቶ ደፈርሻ ወደ ክርስትና እምነት ዘወር ያሉት ብዙ ሳይቆዩ ነበር። ወይዘሮ ማርሴላ ኦህማንም የተዋጣላቸው ሐኪም ስለነበሩ የሁለቱም አገልግሎትና ስም በስፋት ናኘ። አምስተኛው የቡልቂ የሰበካ ጣቢያ በአስተማማኝ ሁኔታ በእግሩ ቆመ።



የመጀመሪያው የቡልቂ ሚስዮን ጣቢያ ምንጭ ፡ Cords of Love

በ1923 መጀመሪያ ላይ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ምድር ምንም አይነት መሬት በርስትነት (ቋሚነት) እንዳይገዛ የሚያግድ ሕግ ነበር። ጂማ ደግሞ በዶክተር ላምቤ የሩቅ ዘመን ሕልም ዋነኛዋ ማእከል እንደነበረች እናም ሚሲዮናውያኑ ገና ከየአገራቸው ሳይነሱ መድረሻቸው ጂማ እንደምትሆን ነበር የተነገራቸው፤ የሚያውቁትም። የእግዚአብሔር ልዩ ጣልቃ ገብነት አስቀድሞ በረከቱ ለደቡብ ኢትዮጵያ እንዲዳረስ አደረገ። ላምቤ ግን ተስፋ የሚቆርጡ ሰው አልነበሩም። ወደ ጂማ ጅሬን ሄደው ከአንድ አርመናዊ ነጋዴ ጥቂት ቤቶች የተሠሩበትን ሰፊ መሬት ገዙ። አርመናዊው መሬቱን የገዛው የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ማንኛውም ሰው ርስት

እንዳይገዛ የሚከለክለው ሕግ ከመውጣቱ አስቀድሞ ስለነበር የባለቤትነት መብቱን ለማስተላለፍ ችግር አላጋጠማቸውም ነበር። ስድስተኛው ጣቢያ መቆናጠጫ ያገኘው በዚህ ሁኔታ ነው።

በመጋቢት ወር 1923 ዓ.ም. ሚ/ር ሮድ በምዕራብ ክፍለ አገራት እንዲሠሩ የተመደቡትን ሚስዮናውያን ይዘው ወደጅማ ተጓዙ። በጂማ ከተቆናጠጡ ከጥቂት ወራት በኋላ በአጋሮ ሌላ ቅርንጫፍ ጣቢያ ለመክፈት ቻሉ። አጋሮና ጂማ ኃይለኛ የሙስሊም ይዞታዎች ስለነበሩ ወንጌልን ለማሠራጨት ቀላል አልሆነላቸውም ነበር ። ነገር ግን የጣሊያን ወረራ ከቦታቸው ሊያፈናቅላቸው ከመቅረቡ በፊት በህዳር ወር 1928 ዓ.ም. ሰባት አማኞች በጂማ ለማስጠመቅ ችለው ነበር።

አዳዲስ ጣቢያዎችን በየዳር አገሩ ከመክፈት ጎን አስቀድመው በተመሰረቱት ዙሪያ ያሉትን ጎሳዎች በወንጌል ለመድረስ ተስማሚ መነሻ ማዘጋጀት የተጀመረው በ1923 ዓ.ም .ነበር። በላምቡዳ ጣቢያ በሃዲያዎች መካከል በመኖራቸው ቋንቋውንና ባህሉን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲለምዱት ምክንያት የሆነላቸው ሚ/ር ዳፍ እና አነን ከሚስዮን ጣቢያቸው ውጭ በካምባታና ሃዲያ ቀበሌዎች መዘዋወርና መመስከር የጀመሩት በሚያዝያ 1923 ዓ.ም. ነበር። በዚሁ ወቅት የዱራሜን፥ የጠምባሮን፥ የአላባን፥ የባደዋቾን፥ እና የሻሸጎን ጓዳዎች ሁሉ በርብረው ለእግዚአብሔር እርሻ ምን ያህል የተመቸ ሕዝብ እንደሆነ ገምተዋል። ባደጎ፥ ኤሬራሞ፥ ቡሾዓና፥ ሶሮ፥ ሸንቆላ፥ ሊሳአና ወንጌል ተሰብኩባቸዋል።በመስክ የወንጌል አገልግሎታቸውም አቶ ገብረማርያምና አቶ ሄሊሶን ጨምሮ ሦስት ወይም አራት ሰዎች በክርስቶስ አምነው ነበር።

የመስክ ጉዞው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ በመጋቢት 1924 ዓ.ም. አስቀድመው በላምቡዳ በተዋወቋቸው ወዳጃቸው በአቶ ሺበሺ አማካኝነት በዱራሜ ሊሰፍሩበት ያለውን ጣቢያ ተመለከቱ። በሕዝቡ ብዛትና ትሑት መንፈስ ልባቸው ተማርኮ ስለነበር አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ አቶ ሙሉነህንና አቶ ሺበሺን ወደ ሥፍራው ልከው ለአገልግሎታቸው የሚመቻቸውን የመሬት ኪራይ ውል ለመፈጸም የመሬቱን ባለቤት አቶ ያምቦን አነጋግረውና ተዋውለው ውሉ በፊርማ የሚጸናበትን ቀን ቆርጠው ተመለሱ። በነሐሴ ወር 1924 ዓ.ም. በቀበሌው ሹም አማካኝነት አቶ ያምቦና ሚ/ር ዳፍ ተፈራረሙ። በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በሃያ ብር ወጪ አንድ ትኩል (ጎጆ) ታነጸ። [26] ትኩል መሥራቱ የይዞታ ባለቤትነትን

ከማስረገጡ በተጨማሪ በመስክ አገልግሎት ሲቆዩ እንዲሁም ወደ ወላይታ ሲወርዱና ሲመለሱ ማረፊያ እንዲሆናቸው ታስቦ ነው። ቦታውን በኮንትራት (በኪራይ) መልክ ከያዙ በኋላ በዱራሜ ቋሚ ሚስዮናዊ ለመመደብ ለምን እንደዘገዩ በዝርዝር ባይታወቅም (በበጀትና በሰው ኃይል ችግር ይመስላል) በየካቲት 29ቀን 1925 ዓ.ም. የሚስዮኑ ባልደረባ ጆን ፊሊፕስ በዱራሜ ጣቢያ ድንኳናቸውን ተከሉ።

አቶ ታምሩ አበሞ "ቤተክርስቲያንና የልማት እንቅስቃሴ" በሚል ርእስ ባዘጋጁት ጽሑፍ የመሬቱ ኪራይ ውሉ የጸደቀው የካቲት 24 ቀን 1923 ዓ.ም. ነው ሲሉ ጆን ፊሊፕስ ደግሞ ዱራሜ የደረሱት መጋቢት 10 ቀን 1924 ዓ.ም. እንደሆነ መዝግበዋል። ምናልባት በአውሮጳ እና በእኛ የዘመን አቆጣጠር መካከል ያለው ልዩነት ያስከተለው መዛባት ሊሆን ይችላል።

ከዱራሜ ጣቢያ መቆርቆር ጋር በተያያዘ አቶ ታምሩ በዚሁ ጽሑፍ የጠቀሱት ሌላ አስደሳች ታሪክ አለ፤ ይኼውም አቶ ያምቦና ሚ/ር ዳፍ የተዋወቁት አቶ ያምቦ የመሬት ግብር ለመክፈል ወደ ከምባታና ሃዲያ ዋና ከተማ ሆሳዕና በመጡበት ጊዜ አቶ ሙሉነህ ቤት በማረፋቸው ምክንያት እንደነበረ አረጋግጠዋል። አቶ ሙሉነህ ደግሞ ከሰብሮና ከሽጉጤ ቀጥሎ ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉ ሰው ስለሆኑ ነበር ከሚ/ር ዳፍ ጋር ያስተዋወቋቸው።

የከምባታው ባላባት ፊታውራሪ በርገኖ አቶ ሙሉነህ መሬታቸውን ለሚስዮን በማከራየታቸው ምክንያት በሰንሰለት አስረው ሲያስጨንቋቸው እንኳን ጸንተው ለመቆም የቻሉት ይኼው የቅድሚያ ትውውቃቸው ረድቷቸው ሳይሆን እንዳልቀረ ይታመናል።

ሌላው የወንጌል ስርጭት ግንባር እንዲሆን የተመረጠው የጋሞ አውራጃ ነበር። ሰልማ በርግስተን እና ሩት ብሬይ የተባሉት ሁለት ሴት ሚስዮናውያን በ1926 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ወደ ጨንቻ ተላኩ። ጨንቻ እንደደረሱም ከአገረ ገዢው የመኖሪያ ቤት ግቢ ብዙም በማይርቅ ቦታ ቤት ተከራይተው የወንጌል ምስክርነትና የሕክምና አገልግሎት ጀመሩ። ሩት ብሬይ ጥሩ የሥራ ልምድ ያላቸው ነርስ ነበሩና አገልግሎታቸው እጅግ ተፈላጊ ነበር። እኒህ ሴት የሕክምና አገልግሎት የሰጡት ለሰዎች ብቻ ሳይሆን አንበሳ ላቆሰላት የደጃዝማች አበበ ዳምጠውን በቅሎ ጭምር ነበር።

ከሁለቱ ሴቶች ሌላ ኦርቫል እና ኬሪ ከርክ እንዲሁም ኒኮላስ ሲምፖኒስ የጨንቻን ሥራ ለማጠናከር በተጨማሪነት ተላኩ ። ሆኖም አገልግሎቱ በአብዛኛው ተስፋ አስቆራጭ ሆኖባቸው ነበር። ከወንጌል አገልግሎቱ መጨፍገግ ሌላ ከ9000 ጫማ በላይ ከፍታ ያለው የጨንቻ ቀዝቃዛ አየር እንዳለ ሆኖ የግቢው ጠባብነት አላፈናፍን ስላላቸው ሚሲዮናዊያኑ የስሜትና የአካል ሕመምተኞች ሆኑ።

ዶ/ር ላምቤ በየጊዜው የደረሳቸውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ የተሻለ ዘዴ ለመቀየስ ወደ ጨንቻ ሄዱ። ደጃዝማች አበበ ከከተማው ዳርቻ ድረስ ለማዳ አንበሶቻቸውን ከአሳዳጊያቸው ጋር በመላክ አቀባበል አደረጉላቸው። በወደዱት ቦታም መሬት በኪራይ ሊይዙ እንደሚችሉ ገለጹላቸው።

ላምቤ ከጨንቻ ጉብኝታቸው ከተመለሱ በኋላ ሚ/ር ዳፍን ወደ ጋሞ ሄደው ከኒኮላስ ሲምፖኒስ ጋር በመሆን " የሾማ " ጣቢያን መሠረቱ። የቦታውን ምርጫ ያፀደቁላቸው ደጃዝማች አበበ ናቸው። የገና ዕለትንም ምክንያት በማድረግም ሁለት መቶ ሹሞቻቸው በተገኙበት ለሚሰዮናውያኑ ታላቅ የራት ግብዣ አደረጉላቸው።


በሲዳማ ሆማቾ ጣቢያ የሚያገለግሉት ግሌን ኬይን እና ሚ/ር ሮድ የጌዲኦን ሕዝብ በወንጌል ለመድረስ በነበራቸው ሸክም ምክንያት ቱቲቲ አንድ ሰፈር ለመቆርቆር በጊዜው የሲዳሞ ጠቅላይ ገዥ ለነበሩት ለራስ ደስታ ዳምጠው ጥያቄ ያቀረቡት በ1924 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ነበር። በ1925 ዓ.ም. የካቲት ወር ላይ ሚ/ር ኬይን እና ጀምስ ሉክማን በተሰኙ ሚሰዮናዊ የመጀመሪያው ቤት በጌዲኦ ቱቲቲ ተሠራ። በዚያም እንዲያገለግሉ ክሊፍ ፈርድ እና መርትል ሚሼል የተባሉ ሚሲዮናውያን ተመደቡ።

በቱቲቲ የወንጌል አገልግሎቱ ሥራ ለጥቂት ጊዜያት ዘግይቶ ነበር። ምክንያቱም ራስ ደስታ ዳምጠው አዲሱን የሲዳማ ከፍለ ሐገር ዋና ከተማ ይርጋ ዓለምን ሲያለሙ የገዛ ራሳቸውን ቤት እንዲሠሩላቸው ስለጠየቁአቸው ነበር። እግረመንገዳቸውን ግን ለሚሰዮኑ የሚሆን ቦታ ይዘውና መኖሪያ ቤቶችን ሠርተው በሰኔ 1925 ሊዮና፥ ግሬጎር፥ ሻሬት የተባሉት ሦስት አገልጋዮች ወደ ሥፍራው ሄደው ወንጌልን መመስከር ጀመሩ።

በዚህ ሁኔታ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ኤስ.አይ.ኤም. ሥፍራ በማስፋትና በመቆርቆር እንቅስቃሴው በጠቅላላው አስር ያህል ጣቢያዎችን ለማደራጀት ችሎ ነበር።

ጣቢያዎቹም፤ በወላይታ (አቶና)፥ በከምባታና ሃዲያ (በላምቡዳ)፥ በዱራሜና በማረቆ፤ በጎፋ (ቡልቂ) ፤ በጋሞ (ጨንቻ) በጓላም (ሾማ)፤ በሲዳማ (ሆማቾ ቱቲቲ እና ይርጋዓለም)፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ በጂማ፥(ጅሬን) ሲሆኑ በጣቢያዎቹ በጠቅላላው አምሳ ስምንት ያህል ሚስዮናውያን በመንፈሳዊና አካላዊ አገልግሎቶች ተጠምደው ነበር።

19. የመስፋፋት ሙከራ በሰሜን ኢትዮጵያ



የላስታ አውራጃ ገዢ ራስ ካሣ ቀድሞ ሮሃ የምትሰኘዋን በጓላም ላሊበላ በመባል የምትታወቀውን ከተማቸውን እንዲጎበኙና በዚያም የማኅበራቸውን ቅርንጫፍ እንዲያቋቁሙ ዶ/ር ላምቤን ጋበዟቸው። ግብዣውን ሳያመነቱ የተቀበሉት ላምቤ የካቲት 16 ቀን 1926 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ወደ ላስታ ጉዞ ጀመሩ። በወረኢሉና በደሴ በኩል አድርገው ከሦስት ሳምንታት አስቸጋሪ የበቅሎ ጉዞ በኋላ ላሊበላ ደረሱ። በጉዞው ወቅት የኤስ.አይ.ኤም . ዓለም አቀፍ ቢሮ ዳይሬክተር ቢንግሃም አብረዋቸው

ነበሩ። ቢንግሃም ኢትዮጵያን ሲነበኙ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን የአሁኑ አመጣጣቸው በደቡብ ኢትዮጵያ የተቀጣጠለውን የወንጌል ብርሃን በአካል ተገኝተው ለማየት ነበር። ነገር ግን ያልተጠበቀው የሰሜን በር መከፈት አዲስ አበባ ከመድረሳቸው ጋር ስለተገጣጠመ ከላምቤ ጋር አብረው ተጓዙ። እንደ ራስ ካሣ ቢሆን ላሊበላ ከተማ አጠገብ ተስማሚ ቦታ እንደሚሰጧቸውና ለሆስፒታል ማሰሪያ ደግሞ ብዙ ሺህ ብር እንደሚለግሡ ቃል ገብተው ስለነበር የላምቤ ተጣድፎ መሄድ በጊዜው የተገባ ነበር።

በላሊበላ እንደተጠበቀው በርካታ የማረፊያ ቦታዎች ለምርጫ ቀርበው ለሚሰዮኑ ሥራ ልባቸው ያረፈበትን በመምረጥ በደብረ ታቦር፥ በባህር ዳርና በደብረ ማርቆስ በኩል አድርገው ወደ አዲስ አበባ የመልስ ጉዞ አደረጉ። በደብረ ታቦር የአውራጃው ገዢ የራስ ካሣ ልጅ ከሆኑት ወንድወሰን ጋር የሚሰዮን ጣቢያ ስለመክፈት ተነጋግረው ነበር ብዙ አልገፉበትም እንጂ።

በደብረ ማርቆስ ተቀማጭ የነበሩት ራስ እምሩ የዚያን ጊዜው የጎጃም ጠቅላይ ግዛት አገረገዥ ነበሩ። ላምቤ ደብረ ማርቆስ ከደረሱ በኋላ ሚያዝያ 1 ቀን 1926 ዓ.ም. (ኤፕሪል 9 1934) ለሥራ ባልደረቦቻቸው በላኩት ሪፖርት ነክ ደብዳቤዎቻቸው ውስጥ ቀጥሎ ያለውን ጠቅሰው ነበር፤

> ... ጉዞው እጅግ አድካሚ ቢሆንም እንኳን አስደናቂ ግን ነበር፤ ረዥም ቀናትን በበቅሎ በመጓዝ አስፈሪዎቹን ወንዞችና ሸለቆዎች ማቋረጥ ነበረብን፤ ሌሊቱ ብርዳማ ነው።... ልነግራችሁ የምወደው ዋናው ቁም ነገር አገረ ገዢው በዚህ (በደብረ ማርቆስ) እና በጣና አካባቢ (ባህርዳር) ጣቢያ የምንቆረቁርበት መሬት ሊሰጡን ፈጽሞ ፈቃደኛ መሆናቸውን ነው።[31]

ዶ/ር ላምቤ ከራስ እምሩ ጋር የነበራቸው ቆይታ ምን ያህል ተስፋ የተሞላው እንደነበረ በሌላው መጽሐፋቸው ሲጠቅሱ፤ "እንደ እኔ ግምት ከሆነ በኢትዮጵያ ምድር ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ መልካሙ ሰው ራስ እምሩ ናቸው። ጨዋ እና ለወዳጆቸው የታመኑ፥ መማለጃ የማይቀበሉ፥ ክፋትም የሌለባቸው ሰው ናቸው። ስለታም ያልሆኑ በጎ አድራጊ መሆናቸውንም ተረድቻለሁ..."[32]

ቢንግሃምና ላምቤ ከሰሜኑ ጥናታዊ ጉዞአቸው እንደተመለሱ ብዙም ሳይቆዩ ግንቦት 6 ቀን 1926 ዓ.ም. የክረምቱ ዝናብ ከመጀመሩ በፊት

ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹን ስድስት ሚስዮናውያን አሰማሩ። ራስ ካሣ እንደገቡላቸው ቃል ቢሆን ኖሮ ሁሉም ነገር በቀና ሁኔታ በሰመረ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር እንዳልጠበቁት ሆነ። እነዚህ "ታቦት" የሌላቸው ሰባኪዎች "በተቀደሰችው ምድራችን" የኮቴ መርገጫ እንኳን ሊያገኙ አይገባቸውም፤ በማለት ካህናቱ ታላቅ አመፅ አስነሱ። ከአመፁው ክፋት የተነሣ በከተማው ውስጥ በተናቀው አልባሌ ሥፍራ እንዲሰፍሩ ተገደዱ።

ይህንን ያልተጠበቀ አመፅ የሰሙት ላምቤ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ወደ ላሊበላ እንደገና መጓዝ ግድ ሆነባቸው። የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን በደረሱ በስምንተኛው ወር የካቲት 1927 ዓ.ም የላስታው ገዢ ራስ ካሣ ላሊበላ ውስጥ የግል ይዞታቸው የሆነውን መሬት ስለስጧቸው ግንባታ ተጀመረ። 1927 ዓ.ም. የማይጨው ጦርነት ዋዜማ ስለነበር ከቀሳውስቱ ኃይለኛ ተቃውሞ ጋር ተደማምሮ የረባ ነገር ሳይሰሩ በ1928 ዓ.ም ከሰሜን ኢትዮጵያ ለመውጣት ተገደዱ።

ከላሊበላ ወደ አዲስ አበባ የመልስ ጉዞ ሲያደርጉ ዶ/ር ላምቤ በደብረ ማርቆስ ጣቢያ እንዲሠሩ የተመደቡትን ሚስዮናውያን ይዘው በማለፍ ከከተማው የአንድ ሰዓት ያህል መንገድ ወጣ ባለ ቦታ ላይ የሚስዮን ጣቢያ ተቆረቆረ። ነገር ግን ከጣሊያን ጦርነት ቀደም ብሎ በተነሣው ሕዝባዊ ያለመረጋጋትና በጓላም በጦርነቱ ምክንያት እንደ ላሊበላ ሁሉ ይኼኛውም ጣቢያ ያለውጤት ተዘጋ።

የሰሜን ክፍለ አገራት ጉዞ በላምቤ ትዝታ ውስጥ የሐዘን ጥላ ከጣሉት ገጠመኞቻቸው ውስጥ የሚደመር ነው። በዚህ በሁለተኛው ጉዞ ላይ እያሉ ነበር ከአዲስ አበባ የተላከላቸውን በርካታ ደብዳቤዎች ከፍተው ሲያነቡ በድንገት የአንድያ ልጃቸውን መሞት የተረዱት። ሐዘኑ በተለይም በመንገድ ላይ አብረዋቸው ለነበሩት ባለቤታቸው የባሰ መራራ ሆነባቸው። በጊዜው የተሰማቸውን ሲጽፉ ላምቤ እንዲህ ብለው ነበር፤

> ከላሊበላ ተነስተን በደብረ ታቦርና በጣና በኩል ዞረን ፖርቹጋሎች በሰሩት አሮጌ ድልድይ ተሻግረን ድንኳናችንን እንደተከልን ለአንድ ወር ያህል ሲያፈላልገን የነበረው አንድ የኦሮሞ ተወላጅ ፖስተኛ ከረጢት ሙሉ ደብዳቤ ይዞልን መጣ።
>
> ደብዳቤውን እየከፈትን ስናነብ የልጃችንን አስደንጋጭ የሞት መርዶ አነበብን። ልጃችን ዋላስ በደቡብ አሜሪካ የሞተው ከአንድ ወር

በፊት ነበር። ... ሐዘኑን ልንቋቋመው አልቻልንም ፤ ብቻ ሰማያዊው አባታችን ይህንንም ደግሞ ከእጆቹ እንድንቀበል ብርታት ሰጠን እንጂ። ለባለቤቴ ምን ያህል ከብዷት እንደነበረ የሚያውቁት ያለፉበት ብቻ ናቸው። እንደምንም ብለን ከሦስት ሳምንት ጉዞ በኋላ አዲስ አበባ ገባን። ተጠርተን ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት በቀረብንበት ጊዜም ከአንደበታቸው ምንም ቃል ሳይወጣ ለአምስት ደቂቃ ያህል እንባቸው ያለማቋረጥ በጉንጫቸው ላይ ይፈስ ነበር። ያም ከቃላት ይልቅ ሐዘናችንን ምን ያህል እንደተጋሩ የሚያስረዳ ነው።"[33]

በጣሊያን ወረራ ዋዜማ ጦርነቱ በይፋ ሳይጀመር በጣሊያኖች የተገዙ ባላባቶችና መሳፍንት ከኩርፊያ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እዚህም እዚያም የሰላም መደፍረስ በታየበት ዘመንና ዶ/ር ቢንግሃም ኢትዮጵያን ለሁለተኛ ዙር በነበሩበት ወቅት የሚሰዮኑን አገልግሎት ቀጣይነት አስተማማኝ ለማድረግ አንድ "ተቀዳሚ" ሰው ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዲኖረው የሚል ሐሳብ አቅርበው ነበር። ይህንን ምድራዊ ዜግነት ስለወንጌል ክብር የመለወጥን ታላቅ መሰዋእትነት ሊከፍሉ የሚችሉ መቼም ያለ ዶ/ር ላምቤ ሌላ ሰው አይጠበቅም። አዎ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ለማግኘት ዶ/ር ላምቤ ማመልከቻ በማቅረብ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው በሕጉ መሠረት በመሐላ ኢትዮጵያዊ ዜግነትን ተቀበሉ።

የላሊበላን ችግር ለማቃለል ለሁለተኛ ጊዜ የሄዱትም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ከተቀበሉ በኋላ ነበር። የኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው ምናልባት መሬቱን በቀላሉ በኮንትራት ለመያዝ መብት ሳይሰጣቸው አልቀረም። የንጉሠ ነገሥቱ ማጽናናትም ምናልባት ከዜግነታቸው ጋር የሚደመር ሳይሆን አልቀረም።

የግርጌ ማስታወሻዎች
ምዕራፍ ሦስት

[1] ጳውሎስ ኞኞ ፣ ዐዲ ቴዎድሮስ ገጽ 174 ።

[2] Paul E. Balisky, WOLAITTA EVANGELISTS ... P. 105.

[3] Albert E. Brant, In The Wake of Martyrs P. 23.

[4] አቶ ሰብሮ ወሰሮ ፣ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ 1988 ዓ·ም·

[5] Peter. F. Cottrell, Born At mid night, P. 12.

[6] Albert E. Brant, In The Wake of Martyrs, P. 16.

[7] Grenstedt Staffan, Ambericho A Remarkable Venture In Ethiopian Christian Solidarity, P. 39.

[8] በወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፣ ያልታተመ ፣ ገጽ 6 ።

[9] በቀለ ገሙ "እንዴት ሊሆን ይችላል ?" ቃለ ሕይወት መጽሔት ፣ ቁ· 8 (መጣጥፍ) 1986 ዓ·ም· ።

[10] Paul E. Balisky, P. 117

[11] አቶ ፈለሃ አዴቶ ፣ አቶ ኪነዶ ጣሌ ፣ ነሐሴ 4 ቀን 1989 ዓ·ም· ከዘጋቢው ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ የተወሰደ ፣ ቁጫ ።

[12] በየነ አንኮቴ ፣ ነሐሴ 3 ቀን 1989 ዓ·ም· ከዘጋቢው ጋር ከተደረገ ቃለ ምልልስ የተወሰደ ።

[13] ዮሐንስ ዳሮታ ፡ ዳልሻ ዳና ሲጎ ፡ ሶሳ ጋይላ ። ነሐሴ 1 ቀን 1989 ዓ·ም· የተደረገ ቃለ ምልልስ

[14] ኩርሴ ሽፈኖ ፡ የጌዲኦ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያልታተመ ፡ 1978 ዓ·ም·

[15] አታራ ገመያ ፡ ነሐሴ 7 ቀን 1988 ዓ·ም· የተደረገ ቃለ ምልልስ ።

[16] ባሕሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ ፡ ከ1848 እስከ 1966 ፡ ገጽ 133 – 134 ።

[17] Reidulf K. Molvaer Black Lions, P. 7

[18] Ibid., P. 23

[19] Raymond J. Davis, Fire on the Mountain, P. 51.

[20] Berhanu Deresee, The History of Kale Heywet Church,

[21] Raymond. J. Davis, P. 30.

[22] Born At midnight, 1973.

[23] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 33

[24] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 34

[25] Albert. E. Brant, P. 295

[26] Born At Midnight. P. 35

[27] Duff C. W., Cords of Love. P. 143

[28] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 31

[29] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 179

[30] ታምሩ አበሞ ፡ በተ ክርስቲያንና የልማት እንቅስቃሴ ፡ 1976 (ያልታተመ)

[31] Duff C. W., P. 229

[32] Born At Midnight P. 77.

[33] Lambie T.A., A Doctor With out A country, P. 229

ምዕራፍ አራት

የመጀመሪያው መከር



የመጀመሪያዋ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በደቡብ ኢትዮጵያ (ሲዳማ)

ምንጭ ፡ Cords of Love

20. ከመከር በፊት

"...እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው? "

(የሐዋ.8:37)

አንድ የባህር ማዶ ጸሐፊ እንደዘገቡት፤ ዓለም ኢትዮጵያውያንን ረስቷቸው እነርሱም ዓለምን ረስተው ለሺህ ዓመታት ተኳርፈው ኖሩ። ዓለምና ኢትዮጵያ በተረሳሱበት ዘመን ቀደም ሲል በሙስሊም ኃይሎች ኋላም በወራሪዎች ከበባ ተዘግታ የኖረችው ኢትዮጵያ ሕዝቧ ሕይወትን ረስቶ ሕይወትም ከሕዝቡ ተካክዳ ሃያኛው ምዕተ ዓመት ገባ። በተራው ሕዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ሕይወት እጅጉን ከብዶ ነበር።

ከአውሮጳና ከአሜሪካም ይልቅ እጅግ ቀድሞ በሰሜን ኢትዮጵያ የተዘራው የወንጌል ዘር ከቤተመንግሥት ወደ ቤተ መንግሥት፥ከአንዱ ስርወ መንግሥት ወደ ሌላው ስርወ መንግሥት ሲንገዋለል በአዲስ ኪዳን አገርኛ ፈሪሳውያን ካባና ጥምጥም ስር ጩቶ በልቶት ቀረ። የነገሥታቱና የመሣፍንቱ፥የመኳንንቱ ወግ እና ግሳመሪያ ሆኖ ቀረ። ይህም ብቻ አይደለም " ክርስትና በኢትዮጵያ የባህል የፖለቲካና የማህበራዊ ሕይወት መጋዘን ሆነ " ኡለንዶርፍ የተባለውን ጸሐፊ ጠቅሰው ኢያሱ ሉልሰገድ በአንድ የጥናት ወረቀታቸው እንደገለጹት።[1]

ክርስቶስ የመሰቀል ላይ ሞቱ የሚታሰብበት ስርዓት ተራ የመብልና የመጠጥ፥ ብድር መመላለሻም ግብጥ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስም የተዘጋ መጽሐፍ ሆኖ ለላንቲካ ብቻ ታጅሎ ተቀመጠ። "ከተራው ሕዝብ " ርቆ የተቀደሰ ቋንቋ ነው እየተባለ የደብተራ አፍ ማሟሻና የተረብ መፈጠሪያ ሆኖ ቀረ። ይልቁንም ምድሪቱ ለውጭው ዓለም በተዘጋችበት ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን የሚተኩ ወይም መጽሐፍ

ቅዱስ የሚመዘንባቸው የተለያዩ የገድሎችና የውዳሴዎች አፈ ታሪኮች ተፈጠሩ። ከውዳሴዎቹ መካከል ነገሥታቱ የደረሷቸውም ነበሩ።[2]

ከዚህ ሁሉ በላይ ከጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ የአስተምህሮት ያለመግባባቶች በተነሱ ቁጥር የመጨረሻው ፍርድ ሰጪ ባለሥልጣን መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ ቀርቶ ነገሥታቱ ሆኑ። የነገሥታቱ ፍርድ ደግሞ ከአገር አንድነትና ከአገዛዝ ፖሊሲ አንጻር የሚዳኝ በመሆኑ በመካከለኛው ዘመን በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ያለው ድንበር ጭራሹኑ ጠፍቶ ነበር። ለምሳሌም ያህል በኤፆስጣቴዎስና በአኖሬዎስ ተከታዮች መካከል የተነሣውን ሃይማኖታዊ ውዝግብ አጼ አምደጽዮን ማሰሪያ ሲያበጅለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብያኔ በመስጠት ሳይሆን አኖሪዎስን አዋርዶ ከገረፈው በኋላ "እናንተ በሃይማኖት ስትጨቃጨቁ አገሬን እንዳትከፋፍሉ ተጠንቀቁ" በማለት ነበር።[3]

ይህ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ጋብቻ ፍቅር በጸናበት ዘመን ኢትዮጵያዊነትና የኦርቶዶክስ ሃይማኖተኛ መሆን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆኑ ። ኢድ የተባለ ጸሐፊ እንደሚለው "የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ የመለጠፏን ያህል መንግሥትም በቤተ ክርስቲያን ላይ የተለጠፈ ነበር። መደጋገፋቸው ደግሞ ፖለቲካዊም ርእዮታዊም ይዘት ነበረው።[4]

ነገሥታቱ የአገርን አንድነት "ከሃይማኖት አንድነት" ለይተው አያዩትም ነበር ። "አገር አቅኑ ... ድንበር አቅኑ ... ድንበር አስፉ!" ሲሉ "ሃይማኖትን አስፋፉ! አረመኔውን አጥምቁ!" ከማለት የተለየ አልነበረም።[5] አቡነ ቴዎፍሎስ በ1969 እ.ኤ.አ. እንደተናገሩትና [5] አንድ ጸሐፊ እንደጠቀሰው:-

"ያለ ቤቶ ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ) መንግሥት ብሎ ነገር የለም፤ ያለመንግሥትም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን አትኖርም። በኢትዮጵያ ውስጥ ቤተክርስቲያንና መንግሥት አንድና አንድ ናቸው።[6]

ከአንድነታቸውም ጽናት የተነሳ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ማዕከላዊው መንግሥት እንደገና ሲያንሠራራ እና በብዙ መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሲበረታ፤ ወደግዛቱ ሲጨምራቸው በሌላም ጊዜ ሲዳከም፥ ሲለቃቸው የነበሩትን የደቡብና ደቡብ ምዕራብ አውራጃዎች እንደገና ለመቆጣጠር ሲችል እያንዳንዱ ፌታውራሪ በረገጠበት ዓይነተኛ መሬት ላይ ሁሉ ታቦት ይተክል ነበር። ተወላጁ ከግዛት ማስፋፋት ጋር አብሮ የመጣለትን እምነት እንደ ገዢዎቹ ኃይማኖት ስለቆጠረው አልፎ አልፎ ቢሆንም የወንጌል እውነት በበራላቸው አንዳንድ ካህናት በኩል እውነተኛው የወንጌል ቃል ቢነገረውም የደቡብ ግዛቶች ሕዝብ ግን ጆሮውንም ልቡንም ለወንጌል ዘግቶ ኖረ። ሆኖም በርካታ የወንጌል መልእክተኞች የመታደስ ዘመን ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነው እንደቀድሞው አገባቡ ሁሉ ከሰሜን ኢትዮጵያ ይሆናል ብለው ተስፋ አድርገው ስለነበር አብዛኛዎቹ የተሰማሩት ወደዚያው ነበር። የገመቱት ሳይሆን ቀረና ወንጌል ሊሰብኩ የመጡት መልዕክተኞች የጦር መሣሪያ ለማምረት ብረት ሲያቀልጡ ኖሩ። በቴዎድሮስ ዘመን በጎንደር ቤተመንግሥት ዙሪያ ስለነበሩት ሚሲዮናውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የመዘገቡት እውነታ እነሆ፤

> ከፕሮቴስታንቶች ጋር ግን ቴዎድሮስ ባብዛኛው ተወዳጅቶ ነበር። ለዚህም በቂ ምክንያቶች ነበሩ። አንዱ የሚያቀርባቸው ቤልና ፕላውዲን ፕሮቴስታንት መሆናቸውና አቡኑም (አቡነ ሰላማ) ቢሆን በልጅነቱ ግብፅ አገር በፕሮቴስታንት ሚስዮን ትምህርት ቤት ተምሮ ያደገ መሆኑ ነው። ከዚያም በላይ የፕሮቴስታንቶች ዓላማ ባብዛኛው ኢትዮጵያውያንን ወደነሱ ዓላማ ከማስኮብለል ይልቅ፥ የአርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ተሐድሶ ለማምጣት መሆኑም በቴዎድሮስ ዘንድ ተቀባይነት አስገኝላቸው። እሱም ራሱ የሚፈልገው ከዚህ የራቀ አልነበረምና። በተጨማሪም ፕሮቴስታንቶች ከስብከት ባሻገር ጠቃሚ የሆኑ የእጅ ሙያዎች እንደ አናጢነትና ግንበኝነት የመሳሰሉ ለማስተማር ዝግጁ መሆናቸውም ጥበብ ለተጠማው ንጉሥ ማራኪነት ነበረው። ከዚህ ሁሉ የተነሣ ቴዎድሮስና ፕሮቴስታንቶች እጅግ ተቀራርበው በጋራ ቁርባን እስከማድረግ ደርሰው ነበር። ማየርና ቫልድማየር የተባሉት ሁለት ሚስዮናውያንም ኢትዮጵያውያንን አግብተው ነበር። ቫልድማየር ዐፄ ቴዎድሮስ ዓለም ሁሉ ከድቶት ብቻውን በቀረበት ጊዜ እንኳ አልተለየውም፥ አገሩን ለማደስ ከእግዚአብሔር የተላከ መስፍን አድርጎም ያየው ነበር።[7]

ሚስዮናውያን ስለ እምነት ወይም የአገር መታደስን በተመለከተ ለዐፄ ቴዎድሮስ የነበራቸው ክብር ፍጻሜው አላማረም ነበር። ባህሩ ዘውዴ እንዳሉት፡- "... እሱ (ቴዎድሮስ) ለደገሰላቸው የመግሪያ ፋብሪካ ሥራ ዝግጁ አልነበሩም " ግን ብረት ማቅለጡ አልቀረላቸውም፤ መራራዋን ጽዋ በግድ ተጎነጨች።

የሚጓጉለትንም መታደስ ሳይመለከቱ በቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ ድርሽ እንዳይሉ በደንብ ተከለከሉ። የስብከት ሥራዎቻቸውም በቤተ እስራኤላውያን (ፈላሻዎች) እና በሌሎች " ያልተጠመቁ ሕዝቦች " ዘንድ ብቻ እንዲወሰን ተደረገ። መቼም ከታሪክ እንደምንማረው ከመጡበት ዓይነተኛ ዓላማ ይልቅ በማይመለከታቸው ጉዳይ ውስጥ እየገቡ መዘዝ የሚጭሩ የባህር ማዶ የወንጌል መልእክተኞች አልጠፉም ነበር፤ ወደፊትም አይጠፉም። በዚያን ጊዜ ከነበሩት መካከል እስተርን የተባለው ሚስዮናዊ በመጽሐፉ ውስጥ ንጉሡን በማንቋሸሹ የቴዎድሮስ ቁጣ ገንፍሎ በሱ የተጀመረው እስራት ለሌሎችም ተረፈ። በዚህም ዘለፋው ሳቢያና በሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች የሰሜኑ ዋነኛ የተሐድሶው ዓላማ ምኞት ብቻ ሆኖ መክኖ ቀረ።

" ዘመኑ በተፈጸመ ጊዜ " በሰው ዘንድ ፈጽሞ የተረሳ ወደመሰለው የደቡብ ክፍል የወንጌል መልእክተኞች በየአቅጣጫው እንዴት እንደተሰማሩ ስላጋጠማቸውም እንቅፋትና ተግዳሮት ባለፉት ምዕራፎች በሰፊው አትተናል። ሰዎች በየዘመናቱ እንዳሰቡት ሳይሆን እግዚአብሔር የወደደው ይፈጸም ዘንድ" ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል" ተብሎ እንደተጻፈ ከ1920ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ፊቱን ዘወር አደረገ።

በአንዳንድ አውራጃዎችና ብሔረሰቦች ወይም ጎሳዎች ዘንድ ወደ ክርስቶስ መንግሥት መመለሱ የተገለጠው በሕዝብ ደረጃ ነበር። ይህም ግላዊ የሕይወት መለወጥ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው። አዘውትረን ባነሳናቸውና ወደፊትም ደጋግመን በምናነሳቸው በሦስቱ ግንባር ቀደም አውራጃዎች(ወላይታ፣ ሲዳማ እና ከምባታና ሃዲያ) ወንጌል ከተሰበከ ከአንድ አመት ተኩል በኋላ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አማኞች

በተቀራረበ ሰሞን የክርስትናን እምነትን ተቀበሉ።[8] ሁለት ዓመት ሳይሞላ ሠላሳ ያህል የወንጌል አማኞች መደበኛ የአምልኮ ቀናት ተሳታፊዎች ሆኑ።

21. የመጀመሪያዎቹ ተጠማቂዎች

እኒያ ቀዳሚዎቹ የወንጌል ፍሬዎች በመንፈሳዊ ዕውቀት እያደጉ በሄዱ መጠን የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንታዘዛለን? በማለት ራሳቸው ጥያቄ መጠየቅ ጀመሩ። የመጀመሪያው ጥያቄ ስለ ጥምቀት ነበር። በመጀመሪያም ጥያቄውን ያነሱት የሲዳማ አማኞች ነበሩ። የጥምቀት ሥነ ሥርዓትን በዋነኛነት፥ ቀጥሎም የበዓል ቀናት አቆጣጠር በፈረንጅ ወይም በአበሻ ይሁን የሚለውን ጥያቄ ለመፍታት የአዲስ አበባውን ጽ/ቤት በማእከልነት ደረጃ ስለማጠናከር የሚነጋገር ጉባኤ ከግንቦት 8 እስከ 10 ቀን 1924 ዓ.ም. ባሉት ሦስት ቀናት በወላይታ ሶዶ ከተደረገ በኋላ ለጥምቀት የተዘጋጁት እንዲጠመቁ ጉባኤው ተስማማ። የማጣራቱን ኃላፊነት በተመለከተ ከሥነ መለኮት አንጻር ሚስዮናውያኑ፥ በአማኞቹ የተመረጡ ሽማግሌዎች ደግሞ ከተግባራዊው የሕይወት ምስክርነት አንጻር ይመዝኑ ነበር። የድርብ ጋብቻ እና የባህላዊው እምነት ልምምዶች ዋነኛ መለኪያዎች ሆኑ። ለመጠመቅ ጓጉተው ከነበሩት ሃያ ያህል አማኞች አራቱ ብቻ ታህሳስ 16 ቀን 1925 ዓ.ም. ዲሴምበር 25 ቀን 1932 የጥምቀት ሥነ ስርዓት በሲዳማ ሆማቾ ፈጸሙ። እነርሱም:- አቶ በኤ ቴሶ፥ አቶ ጠቢሳ ቡንታ፥ አቶ ዴቀሞ ዴቡ፥ አቶ ሲዳ ዴቡ ናቸው። አጥማቂዎቹ ዶ/ር ላምቤ እና ሲዳማን በብርቱ ሲያገለግሉ የነበሩት ሚ/ር ኬይን ነበሩ። በጥምቀት ሥነ-ስርዓቱ ላይ የተገኙትን ዶ/ር ሁፐር የተባሉትን ሰው ጠቅሰው ፒተር ኮትሬል ሲጽፉ፤

> በዕለቱ ሊጠመቅ የተዘጋጀውን አንድ ሰው ቤተሰቦቹ ገና በግለጻ ተነሥተው ግብግብ ገጠሙት። ሚስቱ በወገቡ ላይ ተጠምጥማ "ውሃ ውስጥ ተዘፍቀህ የምትጠመቅ ከሆነ ትቼህ እሄዳለሁ" አለችው። እናቱ ደግሞ እያለቀሱ የሚሉትን የማይሰማ ከሆነ የወራሽነት መብቱን እንደሚነፍጉት አስጠነቀቁት። ወንድሞቹና ሌላው የቤተሰቡ አባል ሁሉ በሩን ጠርቅመው በመዝጋት ወደ ውጭ እንዳይወጣ ከለከሉት።[8]

ያን ሰው ግን ከመጠመቅ ሊያግዱት አልቻሉም ነበር። ይህንን ስናይ የቀደሙት ክርስቲያኖች ስለወንጌል የከፈሉት ዋጋ ምን ያህል ታላቅ እንደነበረ እንረዳለን።



የመጀመሪያው የጥምቀት ሥፍራ (ሶማሃ)



የመጀመሪያው የሲዳማ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተጠማቂ
የአቶ በኤ ቴሶ ልጅ አቶ ላሚሶ በኤ ። ፎቶ ፡– ወ.ዓ

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ውስጥ በቀዳሚ ተጠማቂነት የሚጠቀሱት እነዚህ የመጀመሪያዎቹ አራት ሰዎች መጠመቅ፥ መጽናትና የሕይወት መታደስን የተመለከቱት የሲዳማ አማኞች ለሁለተኛ ጊዜ የመጠመቅን ጥያቄ አቀረቡ። ጥያቄው በቀረበበት ሰሞን በሐምሌ ወር 1925 ዓ.ም.የሲዳሞ የሚስዮን ጣቢያ ኃላፊ ወደ አገራቸው ለእረፍት ተመልሰው ስለነበር ዶ/ር ላምቤም ለሥራ ጉዳይ አዲስ አበባ መቆየት ስለነበረባቸው ሚ/ር ዳፍ ከላምቡዳ ሄደው ለጥምቀት የተዘጋጁትንና የተገባቸውን ሰዎች መርምረው እንዲያጠምቁ ወደ ሆማቾ ተላኩ። ማን ይጠመቅ በሚለው የማጣራት ኃላፊነት ላይ አራቱ ቀዳሚ ተጠማቂዎች ተሳታፊ ነበሩ። ከብዙ አማኞች መካከል ሦስቱ እንዲጠመቁ ተወሰነና በዚያው በሐምሌ ወር መጨረሻ 1925 ዓ.ም የጥምቀቱ ሥርዓት ተከናወነ። የመጀመሪያው የሲዳማ አማኝ ደባቆ ጉንፋሮ የተጠመቁት በዚህ ወቅት ነው። ሥነ ሥርዓቱን ያስፈጸሙት ሚ/ር ዳፍ ስለሁኔታው ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፤

> ... ባለፈው የፈረንጆች የገና በዓል ዕለት አራት የሲዳማ አማኞች ተጠምቀው ነበር። በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉን ሚስዮኖች ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠመቁት እነዚህ አራቱ ናቸው። ሁሉም በእምነታቸው ጸንተው በሕይወታቸውም አድገዋል።... እኔና በሲዳማ ያሉ ሌሎች ሚስዮናውያን እንዲሁም የመጀመሪያዎቹ አራቱ ተጠማቂዎች ሆነን ሕይወታቸውን አጥንተን እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው እንደሌለ ከተገነዘብን በኋላ ሦስቱን አማኞች ለሁለተኛ ጊዜ አጠመቅን። ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ሰባቱ የሲዳማ ክርስቲያኖች እና ሦስቱ ሚስዮናውያን የጌታ ራት በጋራ ተካፈልን። ሥነ ሥርዓቱ በጣም ቀላል ነገር ግን በረከት የተሞላ ነበር።[9]

ከወራት በኋላ ከተጠማቂዎቹ አንዱ የመኖሪያ ቀበሌውን ሆማቾን ለቆ ሃያ እና ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ አዲስ ቤት ሠራ፥ ለአዲሶቹ ጎረቤቶቹም ወንጌልን መመስከር ጀመረ። ዶ/ር ላምቤ እንደሚሉት በመጀመሪያው ላይ የሚመሰክርላቸው ሰዎች እያላገጡ ስላሾፉበት በጣም ተስፋ ቆርጦ ነበር። አንዳንዶቹ ቆሞ እያናገራቸው ትተውት ይሄዳሉ፥ ሌሎችም ይሰድቡታል። ወደ ሆማቾ መጥቶ ተስፋ መቁረጡን ከተናገረ በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ነገር ግን አሁንም መመስከሩን አልተወም ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ ሲመለስ አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ

ግል አዳኙ አድርጎ መቀበሉን የምሥራች ይዞ መጣ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሦስት ነፍሳት ተጨመሩ። ሦስቱ ከተጨመሩ አንድ ወር በኋላ ሰምንት ያህል አመኑ። አሁንማ እንግዲህ ምን እንጠብቃለን? ብለው የጸሎት ቤት መሥራት ጀመሩ። ይቺም ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ (በሲዳማ) የመጀመሪያይቱ ጸሎት ቤት ነች።

በ1926 ዓ.ም. በወላይታ አቶና አካባቢ የነበረው የወንጌል ስርጭት ተቀጣጥሎ የጣዖት አምልኮንና የሰይጣን ገባር የሆነውን ባህላዊ ልምምድ እንደሰደድ እሳት እየበላ ብዙ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መለሰ። አንድ ባንድ፥ በቤተሰብና በትናንሽ ቡድኖች የሚደረገው የወንጌል ስርጭት ወደ ሕዝብ ደረጃ መለወጥ የጀመረው ከሁሉም አውራጃዎች ቀድሞ በወላይታ ነው። መስከረም 26 ቀን 1926 ዓ.ም. ዶክተር ላምቤ ከወላይታ በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለዋል፤

> የትናንትናው ቀን በጣም አስደናቂ ቀን ነበር። በእኛ ግምት አራት መቶ ያህል ሰዎች ቃሉን ሰምተዋል። ትናንት ጥዋት በጸሎት ቤቱ ውስጥ አንድ መቶ ስድሳ ያህል ሰዎች ጥቅጥቅ ብለው ተቀምጠው ነበር። በውጭ ደግሞ የምንናገረውን ለመስማት የሚንጠራሩ ከመቶ በላይ ሰዎች ነበሩ። ለልጆች በተለየ ክፍል ውስጥ ትምህርት ተዘጋጅቶላቸው ነበር።
>
> ከሰዓት በኋላ እንደገና በርካታ ሕዝብ መጥቶ ቃሉን ሰማ። እንዲህ ያለውን መነሳሳት ያሳየን የሰማይ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤ ገናም ከዚህ የበለጠ እንዲያሳየን እንጸልያለን ብዙዎች ይጠመቁ ዘንድ ራሳቸው እየጠየቁ ነው። ከንፉ እንደተመለሰን አቶና ካሉት ሚስዮናውያንና ከሚ/ር አህማን ጋር ሆነን ለጥያቄያቸው መልስ እንሰጣለን።[10]

ላምቤ ይህንን ደብዳቤ የጻፉት ወደጎፋ እየተጓዙ በመንገድ ላይ ሆነው ነበር። ከወላይታ የመጀመሪያ አማኞች መካከል አማርኛ አጣርተው የሚናገሩና የሚያነቡ ስለነበሩ መጽሐፍ ቅዱስን በግላቸው አጥንተው ለመጠመቅ መጠየቃቸው ብዙዎቹን ደስ ያሰኘ ነበር። በህዳር ወር 1926 ዓ.ም. ሃያ ሦስት ሰዎች ራሳቸውን ለጥምቀት አዘጋጁ። ወቅቱ የሚስዮኑ ዓመታዊ ጉባኤ የሚካሄድበት ጊዜ ስለነበር ብዙ ሚስዮናውያን በተገኙበት

ስብሰባ ተደርጎና መሠረታዊ የክርስትና እውቀታቸውን የሚመዝኑ ጥያቄዎች ከቀረበላቸው በኋላ አስራ ሦስቱ ለጥምቀቱ ብቁ መሆናቸው ተረጋገጠ።

ነገር ግን እንደ ሲዳማ ሁሉ በወላይታም ትክክለኛውን ግጣራት ሊያደርጉ የሚችሉት የአገሬው ተወላጆች እርስ በርስ ተወያይተው መሆን እንዳለበት ያስመሰከረ አንድ አጋጣሚ ተከሰተ። ሁኔታውን ሬይመንድ ዴቪስ እንደሚከተለው መዝግበውታል፤

> አቶ ደስታ ተነስቶ ለጥምቀት ዝግጁ ወደሆኑት አስራ ሦስት አማኞች ተመለከተ። እኛ እነዚህን ፈረንጆች እናታልል ይሆናል ጥቂቶቻችንም እርስ በርሳችን እንሸነጋገል ይሆናል። ሁላችንም ግን እግዚአብሔርን ማታለል አንችልም። አንዳንዶቻችን ጋያ ማጨስ ትተናል። ነገር ግን በጓሮአችን ትምባሆ መትከልና ለሌላው መሸጥን አልተውንም። አንዳንዶቻችን የሚያሰክር ጠላ ቦርዴ መጠጣት አቁመናል፥ ነገር ግን በቤታችን እያስጠመቅን መሸታ መሸጥ አልተውንም፥ ታዲያ ግንን ነው የምናታልለው? ..... ወደ ሚስዮናውያን ዘወር ብሎ እናንተ ለጥምቀት ምን ያህል ዝግጁ እንደሆንን መርምራችሁናል፤ ራሳችንን ብንመረምር ቅር ይላችኋልን? [11]

ሚስዮናውያኑ የአቶ ደስታን ጥያቄ በአድናቆት ከተቀበሉ በኋላ ውጤቱን በናፍቆት ጠበቁ። የአማኞቹ ውይይትና የጊዜው ውሳኔ ምንነት ሊመስል ይችላል። ነገር ግን በጊዜው ክርስቶስን ለመከተል በወሰነውና ገና በሚወለውለው መካከል ደግቅ መስመር ወይም ድንበርን የከለለ ጥብቅ ውሳኔ ነበር።

ለክርስቶስ ሕይወት ለመለየት ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ለማዳበር በመሸታና በጋያ ላይ የተወሰደው እርምጃ ወደ ሌሎችም ባህላዊና ማኅበረሰባዊ ልማዶች ተሸጋገረ። ለምሳሌ በወላይታ ባህል አንድ ልጅ ተወልዶ አድጎና ጎልምሶ ኃላፊነትን ለመረከብ መድረሱን የሚያስመሰክረው የግዝረትን ሥርዓት በመፈጸም ነው። ለዚህም ነው በወላይታ ወጣቶች እንጂ ሕጻናት የማይገረዙት። በመንፈሳዊ ይዘቱ ደግሞ ያልተገረዘ ወንድ ልጅ ለአግልክቱ መሥዋዕት ሊያቀርብም ሆነ ሊያጥን አይችልም። በመሠረቱ አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነ በኋላ ከአግልክት ጋር ጉዳይ ስለማይኖረው ከላይ የቀረበው ሐተታ አይመለከተውም። ነገር ግን ያልተገረዘ ወንድ ወይም

ሴት የተገረዘ ሴት ወይም ወንድ ሊያገባ ስለማይችል ባህሉን ተሸክሞ ለመጓዝ ለጥንቷ ቤተክርስቲያን ሥራ የሚያበዛባት ሆነ። ይህንን ባህላዊውን ድንጋጌ በመሸሽ ለጥምቀት ራሱን የሚያዘጋጅ ማንም ሰው ባህላዊውን የግርዘት ስርዓት እንዳይፈጽም አማኞች ተስማሙ።

ለመጠመቅ ከተዘጋጁት መካከል ለሦስቱ አዲሱ ውሳኔ አልተዋጠላቸውም ነበርና ራሳቸውን አገለሉ። አሥር ብቻ ቀሩ። ታህሳስ 1 ቀን 1926 ዓ.ም. (ዲሴምበር 10 ቀን 1933) የመጀመሪያዎቹ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አማኞች የጥምቀት ሥርዓት ፈፀሙ። በዚህ ታሪካዊ ዕለት አጥማቂዎች የነበሩት አርል ሉዊስና ሚ/ር አህማን ነበሩ። የጥምቀት ሥርዓቱ በዚያው በኦቶና ሚስዮን ግቢ ውስጥ በተዘጋጀ ሥፍራ ተፈፀመ። የመጀመሪያዎቹ የወላይታ ተጠማቂዎች ስምንት ወንዶችና ሁለት ሴቶች ሲሆኑ ስማቸውም አቶ ደስታ እና ባለቤታቸው ወይዘሮ ማሚቴ፥ አቶ ጮራሞ፥ ባለቤታቸው ወይዘሮ ፓካሬ፥ አቶ ዲያሣ፥ አቶ አሬቦ፥ አቶ ብሩ፥ አቶ ዋንዳሮ፥ አቶ ጎዳና እና ካዎ ቃባ ይባላሉ። ከሁለት ሳምንት በኋላ ሁሉም ክርስቲያኖች የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ተካፈሉ።



የመጀመሪያዎቹ የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተጠማቂዎች

በሲዳማና በወላይታ የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያን አማኞች ከተጠመቁ በኋላ የድካማቸውን ፍሬ ለናፈቁት የወንጌል መልእክተኞች ብዙ ምስጋናና ደስታ ሆነላቸው። በከምባታና ሃዲያ ላምቡዳ የተመደቡት ሚስዮናዊ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲጽፉ፤

በላምቡዳ የአማኞች ጥምቀት በሚያሳዝን ሁኔታ ተጓተተ። እንዴት እንደዘገዩ መናገሩ ምናልባት የሚያከራክር ይሆናል። በእኔ ግምት ግን ሬግ፥ሜሪ እና እኔ ስለ ጥምቀት ለማስተማር ጊዜው እንደደረሰ አስበን ስንወስንና ማስተማርም ስንጀምር ከዚህ በፊት ከምናደርገው በተለየ ሁናቴ በአእምሯችን ስሌት ያከናወንነውና አንዳንዶቹንም አማኞች ወዲያው እንዲቀበሉት መገፋፋታችን አስቆጥቷቸው ሳይሆን አይቀርም።[12]

ከዚህም የተነሳ ሳይሆን አይቀርም እንደሚጠመቁ ከሚጠበቁት አስቀድመው ወንጌልን ከተቀበሉት ወጣቶችና ጎልማሶች ቀድሞ አያጎ ባምቦሬ ሚያዝያ 14 ቀን 1926 ዓ.ም .የተጠመቀው። ይህም ደግሞ የአቶና ጥምቀት ከተፈፀመ ከአራት ወራት ከ14 ቀናት በኋላ መሆኑ ነው። አያጎ ባምቦሬ (በኋላ አሰፋ የተባለው) የከምባታና ሃዲያ ሚስዮን ብቸኛ ተጠማቂ ሊሆን እንዴት እንደቻለ አሁንም በጥቂቱ ማብራራት ያስፈልጋል፡፡

አቶ አያጎ ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለው በሚስዮን ጣቢያ ተቋቁሞ በነበረው የመሠረተ ትምህርት ጣቢያ ፊደል ለመቁጠር ሲመላለስ በነበረበት ወቅት ነው። ትምህርቱን ለመቀጠል በነበረው ታላቅ ጉጉት ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በስዊድሽ ሚስዮን ት/ቤት ሊገባ ቻለ። በዚያም መንፈሳዊ ሕይወቱ በጣም ተለወጠ። የጥምቀት ስርዓት እንዲፈጸምለት ሲጠይቅ ክርስቶስን ባመነበት ቦታ ቢጠመቅ ብዙ ምስክርነት ሊኖረው እንደሚችል ስለመከሩት ለክረምት እረፍት የሚዘጋበትን ቀን እየጠበቀ ዓመቱን በአዲስ አበባ አሳለፈ። ወደ ላምቡዳ ሲመለስ የጠበቀው ሁሉ ሊሆንለት አልቻለም። ሚስዮናውያኑ በዚያ አልነበሩምና። ክረምቱ አልፎ መሰከረም ሲጠባ አዲስ አበባ ተመልሶ ለዶክተር ላምቤ ታሪኩን አጫወታቸው። በወገኖቹ መካከል መጠመቁ መልካም ምሳሌነት እንዳለው ስላመነበት ደብዳቤ አሲዘው ወደ ላምቡዳ እንደገና እንዲመልሱት ዶ/ር ላምቤን ጠየቃቸው።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ያህል የደርሶ መልስ ጉዞ ያደረገው አያጎ (አሰፋ) ላምቡዳ ሲመለስ እግሮቹ አባብጠውና ፈንድተው ነበር። ላምቡዳ ከደረሰ በኋላ ለጥምቀት ዝግጁ መሆኑን የሚያረጋግጡ በርካታ ጥያቄዎች በዘመኑ በነበሩት አማኞች ፊት በግልጥ ቀረበለት። የአገሬው ተወላጆችም የየራሳቸውን ጥያቄ እንዲጠይቁት በቂ

ጊዜ ተሰጣቸው። አሰፋ ለሁሉም በሚያጠግብ ሁኔታ መለሰላቸው። በብዙዎች ፊትም ተጠመቀ።

ይህ ሰው ጣሊያኖች አገራችንን ከወረሩ በኋላ የካቲት 12 ቀን 1930 ዓ.ም. ስድስት ኪሎ በተፈፀመው ጭፍጨፋና አፈሳ ሳቢያ ታስሮ ወደ ሶማሊያ ከተወሰደ በኋላ በዚያው በባዕድ አገር ሕይወቱ አልፋለች። ከሃዲያ ወገን የመጀመሪያው ተጠማቂ ክርስቲያን ሕይወቱ በባዕድ ምድር አለፈች።

ወደ ጀመርነው የጥምቀት ጉዳይ እንመለስና የአሰፋ መጠመቅ በከምባታና ሃዲያ ሚስዮናውያኑ እንደጠበቁት ተአምራታዊ መነሣሣት አልፈጠረም። ከአንድ ዓመት በኋላ በሁለተኛው ዙር የተጠመቀው አሁንም አንድ ሰው ብቻ ነበር።

ግንቦት 6 ቀን 1927 ዓ.ም. በላምቡዳ የተጠመቀው ይህ ሰው ቀዳሚ ዕድል ደረሰው እንጂ ከመጀመሪያዎቹ አማኞች የሚደመር አልነበረም። ስሙ ሊሬሶ ቄቆ ይባላል። ሊሬሶ በተጠመቀበት ቀን ግን ሃያ ሁለት አማኞች ሥነ ሥርዓቱን ተካፍለው ነበር። በአንድ ዓመት የጊዜ ስፋት ሁለት ሰዎች በሃዲያ ሲጠመቁ ሥራው ዘግይቶ በጀመረው በጎፋ ግን ሦስቱ ወንድማማቾች፤ ሳካ፥ ሳንኩራ እና ሲምቡሩ የተባሉት በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም. የጥምቀት ሥርዓት ፈጸሙ።

በማረቆ ጣቢያ ግን መቼ እንደተጠመቀ የሚያስረዳ መረጃ አልተገኘም። ነገር ግን ሕግና ሥርዓት በተፋለሰበት በኢጣሊያን ወረራ ወቅት ማረቆ ጣቢያ ሲያገለግሉ የነበሩት ሁለት ልጃገረድ ሚሲዮናውያን በወረበሎች ተደብድበው ተዘረፉ። ቤት ንብረታቸውም እንዳልነበረ ሆነ። ከአማኞች አንዱ የሆኑት አቶ ደምበል ቤታቸው የሠላሳ ደቂቃ ያህል መንገድ ራቅ ስለሚል አደጋው በደረሰባቸው ምሽት ሚስዮናውያኑን ሊያድኗቸው አልቻሉም ነበር።

በማግስቱ ጠዋት ግን ወደ ተደብዳቢዎቹ ሚስዮናውያን ዘንድ በመሄድ ወደ ቤታቸው በማምጣት የራሳቸው መኝታ ቤት የሆነችውን ጎጆ ቤት ሰጥተው ለሦስት ሳምንታት ያህል አኖሯቸው።

የአገሪቱ ፀጥታ መበላሸት ተስፋ ያስቆረጣቸው አቶ ደምበል ሰላም ይመጣል ብለው ከመጠበቅ ይልቅ ልጃገረዶቹን የኢትዮጵያን የባህል ልብስ አልብሰው ሌሊት ሌሊት በዘወርዋራ መንገድ እየመሩ አዲስ አበባ ለማድረስ ቆረጡ። ከብዙ ፈተናም በኋላ አዲስ አበባ ገቡ።

በአዲስ አበባ ቢሮ የነበሩት ሚስዮናውያንም ለዚህ መልካም ተግባርዎ የሚሆን ምን መልካም ነገር እናደርግልዎት ብለው ሲጠይቋቸው አቶ ደምበል የሰጡት መልስ " ምንም ነገር አልፈልግም . . . ብቻ የጥምቀት ስርዓት ፈጽሙልኝ "ነበር። ብዙም ቀናት ሳይቆዩ በዶ/ር ላምቤ እጅ ግንቦት 30 ቀን 1928 የጥምቀቱ ሥርዓት ተፈጸመላቸው። አቶ ደምበል ምንም እንኳን በሚስዮን እጅ ባይማሩ ለብቻቸው ጌታ ያስተማራቸው መንፈሳዊ እውቀት ለሚስዮናውያኑ ብርቅና ድንቅ ነበር የሆነባቸው። አቶ ደምበል ክርስቶስን አምነው ሕይወታቸውን ያስረከቡት ሚስዮን ግረቆ ከመግባቱ አስር አመት ቀደም ብሎ መጽሐፍ ቅዱስን በግላቸው ሲያነቡ ከመንፈስ ቅዱስ በተገለጠላቸው እውነት መሆኑን በቀዳሚዎቹ ምዕራፎች አውስተናል።

አቶ ደምበል ለግረቆ ሚስዮናውያን ያደረጉትን በጎነት የሰማው የእንግሊዝ ሌጋሲዮንም አስጠርቶ ሁለት መቶ ብር ሽልማት ሰጥቷቸዋል። እኒህ ሰው የሚስዮናውያኑን ሕይወት በማትረፍና በመንከባከብ በኩል ባለውለታና ባለታሪክ ናቸው።

በጂግ የሚስዮን ጣቢያ ደግሞ ጣሊያን በገባበት ዓመት ነሐሴ 1928 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ አራት ሰዎች ተጠመቁ። በ1929 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ሌሎች አራት ሰዎች ለሁለተኛ ጊዜ የጥምቀት ሥርዓት ፈጽመዋል። ሚስዮናውያን ከአገር እንዲወጡ ጣሊያኖች እጅግ ግፊት በሚያደርጉበት በ1929 የመጀመሪያዎቹ ወራት ከከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን አቶ ሽጉጤና አቶ ሬጣቦ በሶዶ (አቶና) የጥምቀት ሥርዓት ፈጸሙ። በሶዶ የተጠመቁበት ምክንያት ሚስዮናውያኑ ከላምቡዳ እንዲወጡ በተገደዱበት ወቅት ሶዶ ድረስ አጅበዋቸው በሄዱበት አጋጣሚ ነበር።

ከሁሉም በላይ የሚገርመው ግን በጣሊያን ወረራ ምክንያት ሚስዮናውያኑ ከየጣቢያቸው ለቀው በወጡ በጥቂት ሳምንታትና ወራት


ውስጥ ከየአቅጣጫው የተሰማው ሪፖርት አበረታች ነበር። ቀዳሚው የምሥራች የመጣው ከወላይታ ነበር። በሐምሌ ወር 1929 ዓ.ም. በአንድ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ላይ ሃያ ሦስት ሰዎች መጠመቃቸው የሚያስደንቅ ነገር ሆነ። ይህም የተጠማቂዎችን ቁጥር ሰባ ሦስት አደረሰው።

በዚሁ ወር ሦስት ተጨማሪ የከምባታና ሃዲያ አማኞች በአዲስ አበባ ተጠመቁ። ስማቸውም አቶ ሺበሺ፥ አቶ ደሳለኝ፥አቶ ሎታ ይባላል። በ1930 ዓ.ም .በጥቅምት ወር ሌላ የምሥራች ከወላይታ ወደ አዲስ አበባ ደረሰ አስራ አራት ሌሎች ተጠምቀው ነበርና።

22. የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም

አዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን እንደ አበባ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ፈክታ ብትታይም አበባውን የሚያራግፍ የመከራ ዶፍ ሊዘንብባት ደመናው እየተጫጫናት ነበር። የወንጌሉን ዘር በስብከት ሞኝነት የዘሩት ሚስዮናውያን ከየጣቢያው እየተገደዱ ሲወጡ በዚህ የመከራ ዋዜማ ላይ እያበበች ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ለአንዳንዶቹ እጅግ ጭንቅ ሆኖባቸው ነበር። አንዳንዶች ደግሞ አበባው ቢረግፍም ፍሬው እንደገና ተበትኖ፥ አንዱም መቶ፥አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሰላሳ ፍሬ እንደሚሰጥ ሁሉን በሚችል አምላክ ታምነው ነበር። በሲዳማ፥በወላይታ፥በከምባታና ሃዲያ፥ በማረቆ፥ በጂማ፥ በጋሞ፥ በአዲስ አበባ ያሉት ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ቢቆጠሩ በሙሉ ከአንድ መቶ አይበልጡም ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል በዘመኑ ብርቅ ነበር። እንኳንስ ወንጌልን ሰምቶ ለማያውቀው ሕዝብ ቀርቶ የደቀ መዛሙርት፥ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፥ የመንበረ ማርቆስ ወራሲ ነን ለሚሉት እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ የተዘጋ መጽሐፍ ነበር። በእርግጥ በግዕዝ፥ በአማርኛ፥ በኦሮምኛና በትግርኛ ቋንቋዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ተተርጉመው ነበር። ስርጭቱ ግን ውሱን ከመሆኑም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ፡በእጃቸው የገባው እንኳን ከገድላ ገድሎችና ከተአምራት መጻሕፍት ለይተው አያዩትም ነበር።



አቶ ጎባ ጎታ ከመጀመሪያዎቹ የጋሞ ወንጌላውያን አንዱ

ፎቶ ፡- ወ.ዓ

ለተራው ሕዝብ ብርቅና ድንቅ የሆነው ሕያው ቃል ለሁሉም ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ እንዲደርስ ለማድረግ ቀዳሚዎቹ የወንጌል መልእክተኞች የጣሉት መሠረት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። ከሁሉም አስቀድሞ የግርቆስ ወንጌል በጎፋ ቋንቋ ተተረጎመ። የጎፋ ቋንቋ ከወላይትኛ ቋንቋ ጋር ጥብቅ ዝምድና ስላለው በወላይታ ዙሪያ ያሉ አውራጃዎች ሁሉ ሊጠቀሙበት ችለዋል። ተርጓሚው ሚ/ር አህማን ሲሆኑ በሰኔ 1925 ዓ.ም. ለሕትመት ዝግጁ መሆኑን ዶ/ር ላምቤ በጻፉት ደብዳቤ አስታውቀው ነበር።

ሌላው የሲዳማ ሚሲዮናዊ ሚ/ር ግሌን ኪይን ይኸንኑ የግርቆስ ወንጌል ከአራት የሲዳማ አማኞች ጋር በመተባበር ተርጉመውት በዚሁ አመት በ1925 ዓ.ም. ታትመ። በወላይትኛ ቋንቋ የዮሐንስ ወንጌል በወቅቱ የተተረጎመ ቢሆንም ሕትመቱ ከመከናወኑ በፊት ግን በጣሊያኖች ወረራ ምክንያት ተሰናክሎ ቀርቷል። ኪሊፎርድ ሚሼል በጉጂ ኦሮሚኛ ከወንጌላቱ አንዱን ተርጉመው ነበር። በጣሊያን ወረራ ወቅት ከሌላው ሚስዮናዊ ቶም ዴቨር እና ሃያ ያህል መንገደኞች ጋር ወደ አዲስ አበባ ሲጓዙ በረሐ ውስጥ በወንበዴዎች ተገደሉ። የተተረጎመውም መጽሐፍ በዚያው ደብዛው ጠፋ።


የማቴዎስ ወንጌል በሚ/ር ዳፍ አማካኝነት በሃዲያ ቋንቋ ተተርጉሞ በ1928/29 በሙከራ ሕትመት ታትሞ ለዘመኑ አማኞች ተሰራጭቶ ነበር። የዮሐንስ ወንጌልም እንዲሁ በሚ/ር ካውዘር አማካይነት ወደ ሃዲያ ቋንቋ ተመልሶ ነበር፥ በጦርነቱ ወቅት ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ ሲሰደዱ ከጠፉት ወይም ከወደሙት ንብረቶች አንዱ የመሆን ዕጣ ገጠመው።

ከዚህ በተጨማሪ በወላይትኛ ቋንቋ "እግዚአብሔር ሲናገር" በሚል ርእስ አነስተኛ መጽሐፍ ታትሞ ነበር። የመጽሐፏ ገጽ ውሱን ቢሆንም የጊዜውን መልእክት የያዙ የምርጥ ንባባት ስብስብ ስለነበረች በብዙ የጥንት አገልጋዮች ዘንድ ተወዳጅ ነበረች።

ለጅማ ክርስቲያኖች ደግሞ ከዓመታት በፊት በአናሲሞስ ነሲብ (የወለጋ ተወላጅ) የተተረጎመ የኦሮሚኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስላላቸው አሳሳቢ አልነበረም። በሁሉም የኢትዮጵያ አውራጃዎች ደግሞ ፊደል የቆጠሩት ወይም በከተሞች ዙሪያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ

ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በብዛት ባይሆንም እንኳን በቀላሉ ያገኙ ነበር።

ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ባልታሰበ ሁኔታ በቅላ የጨለማው ገዢ በሰለጠነበት ምድር አዲስ ኃይል ሆና ለመቆም የቻለችው ከላይ በጠቀስናቸው በእኒህ በተወሰኑ የቅዱሳት መጻሕፍት አቅርቦት ብቻ ነበር ለማለት ባያስደፍርም በዚህ ታላቅና ዘላለማዊ አጀንዳ ውስጥ የእግዚአብሔር አምላካችን ተአምራዊ እጅ እንደነበረበት ግን ለማመን አያዳግትም።



"እግዚአብሔር ሲናገር" በቅድሚያ ከተዘጋጁት የወላይትኛ የትርጉም ሥራዎች አንዱ

ምንጭ ፡ Fire on the mountain

የግርጌ ማስታወሻዎች ምዕራፍ አራት

[1] Eyayu Lulseged, Why do the Orthodox Christians in Ethiopia identify their Faith with Their nation, Proceedings of the first National Confarence.... P. 4.

[2] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋፅኦ ፡ ገጽ 70 ።

[3] Church and State in Ethiopia , P. 208

[4] Eide, Revolution and Religion in Ethiopia, P. 35

[5] የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 – 1966 ፡ ገጽ 51 ።

[6] Eide, P. 33

[7] የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 1966 ፡ ገጽ 41 ።

[8] Birhanu Deresse, P. 31

[9] Cords of Love, P. 271-72


[10] Ibid., P. 272-273

[11] Fire on the mountain, P. 71

[12] Cords of Love, P. 273-274

ምዕራፍ አምስት

ቤተ ክርስቲያን በጣሊያን ወረራ ዘመን



"የኢጣሊያ ምሥራቅ አፍሪቃ ካርታ" (1928 – 1933)

ምንጭ ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ

23. አጠቃላይ እይታ

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ የኢጣሊያ ፋሽስቶች የመንግሥቱን ሥልጣን የጨበጡበት ወቅት ነበር። የአውሮጳ ኃያላን መንግሥታት ከኢትዮጵያና ከላይቤሪያ በስተቀር መላውን የአፍሪቃ ክፍለ አህጉር ተቀራምተው በቅኝ ግዛትነት በያዙበት በዚያ ወቅት የፋሽስት ጣሊያን መሪዎችም "የጥንታዊት ሮማ" ገናናነታቸውን የሚያድሱበት ጊዜ እንደደረሰ ያምኑ ነበር።

ከዚያ ሁሉ በፊት ግን በዳግማዊ ምኒልክ አዝማችነት በ1888 ዓ.ም. አድዋ ላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ተመትው የተዋረዱበትን ውርደት ለመበቀል ለአርባ ዓመታት ያህል ረቂቅ ዝግጅት እያደረጉ ቆይተው በጎዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም በምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍል በወልወል ጠብ የመጫሪያ ጦርነት ለኮሱ። በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥንካሬ የተፈለገውን ያህል ሆኖ የእነሱን ወረራ እንደማይቋቋም በደንብ የተገነዘቡት ጣሊያኖች መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም. መረብን ተሻግረው ይፋ ጦርነት ከፈቱ።

ጦርነቱ በተጀመረ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዐድዋ፥ አዲግራት፥ መቀሌ በአይሮፕላን እየተደበደቡ በወራሪው እጅ ወደቁ። በመጨረሻም ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው የተሳተፉበት የመጨረሻው ጦርነት መጋቢት 22/ 1928 ዓ.ም. በማይጨው ተደረገ። ከአሥራ ሦስት ሰዓት መራራ ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ተበተነ። "ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባ በፋሺስቶች እጅ ወደቀች"[1] ብሎ መፎከሩ የሚነገርለት ግራዚያኒ ደግሞ በደቡብ ምሥራቅ በኩል የነበረውን ጦር እየመራ በሚያዝያ ወር ሐረርን ከተቆጣጠረ በኋላ ያለምንም አቻ ተግዳሮት ወደ መሐል አገር ዘለቀ። የጦር

ሚዳው ፍልሚያ አላዋጣ ያላቸው ኃይለ ሥላሴ ለዓለም መንግስታት አቤቱታ ለማቅረብ ወደ አውሮጳ ተሰደዱ።

ንጉሠ ነገሥቱ ተሰደው ከአገር የወጡት ሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም. ነበር። የንጉሡ መሰደድ ከተሰማ በኋላ መልክ የሌለው ጦርነት በገጠርና በከተማ ተስፋፋ።

> ጅምላ እብደትንና እንጭጭ የመደብ ጦርነትን ያዋሐደ፥ ተስፋ መቁረጥና እምቢተኝነት የተቀላቀለበት እንቆቅልሽ ነበር። ተኩሱም ሆነ ዝርፊያው ዒላማ አለው ከተባለ ዒላማዎቹ ሐብታሞችና የውጭ አገር ኗሪዎች ነበሩ። ቤተ መንግሥቱም ቢሆን በውስጡ ያለው መሣሪያ ተፈላጊ ስለነበር ከዝርፊያው አልዳነም። የውጭ አገር ዜጎች እንዲህ ያለ ነገር መምጣቱ አይቀርም ብለው ለረጅም ጊዜ ራሳቸውን ሲያዘጋጁ በቆዩበት ሌጋሲዮኖች ተጠልለው መዓቱን አሳለፉ። ዞሮ ዞሮ ግን ሁከቱ እንደማናቸውም ተመሳሳይ ሁከቶች ሁሉ እውር ነበር ለማለት ይቻላል። ጠላትና ወዳጅ የሚለይ አልነበረምና።[2]

ጦርነቱ እንደማይቀር የብዙዎች የዘመኑ አዋቂዎች የሚጋሩት ስጋት በሆነበት የ1927 ዓ.ም. የመጨረሻው ወራት ዶ/ር ላምቤና ባለቤታቸው በእንግሊዝና በአሜሪካ ዕረፍትና የሥራ ጉብኝት ሊያደርጉ ከመሄዳቸው በፊት ንጉሡን በግምባር አግኝተው አነጋግረዋቸው ነበር። ንጉሡ የጦርነቱ አይቀሬነት የፈጠረባቸውን ጭንቀት ሲያዋዩአቸው ላምቤ ደግሞ ለክፉም ለደጉም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ተቋቁሞ አገልግሎት የሚጀምርበትን መንገድ ጠቁመዋቸው ነበር።

ላምቤ አሜሪካን አገር በነበሩበት ወቅት ከኃይለ ሥላሴ አስቸኳይ መልእክት ደረሳቸው፥ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ። በመስከረም መጀመሪያ 1928 አዲስ አበባ ደረሱ። ከዐጼ ኃይለ ሥላሴ ጋር በተገናኙም ጊዜ የቀይ መስቀል ማኅበርን እንዲያቋቁሙ አዘዟቸው። ላምቤ በዚህ ወቅት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ስለነበራቸው የማይበገረውን የፊውዳላዊ ቢሮክራሲ በር ሁሉ ለማንኳኳት ባለሙሉ መብት ነበሩ። በሚያስገርም ፍጥነት አስራ ስድስት የተሟላ የህክምና ቡድን በአጭር ጊዜ ውስጥ አቋቋሙ። የመጀመሪያው የቀይ መስቀል ፕሬዚዳንት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ

ሲሆኑ ዶ/ር ላምቤ ደግሞ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ዋና ጸሐፊ በመሆን ሥራውን በቅልጥፍና መምራት ጀመሩ።

ላምቤ ይህንን የነፍስ አድን አገልግሎት በተረከቡ ማግስት የኤስ. አይ. ኤምን ጉባኤ ጠርተው የሚስዮኑ ሥራ እንዳይበደል ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮችን መምረጣቸውን አሳወቁ። የተመደቡት ሁለት ረዳቶቻቸው አንደኛው ሚ/ር ዳፍ የጽ/ቤቱን ሥራ እንዲያከናውኑ፥ ሁለተኛ ሚ/ር ግሌን ኬይን ደግሞ የመስክ አስተባባሪነቱን እንዲመሩ ኃላፊነቱን ተረከቡ።

24. የሚስዮናውያን መባረር

ጦርነቱ ከሰሜን፥ ከደቡብና ከደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫዎች በተፋፋመበት ወቅት የጠቅላይ ግዛት ገዢዎችና፥ ተሰሚነት የነበራቸው የአገር ሽማግሌዎችና ባላባቶች ወደ ጦር ግምባር መዝመታቸው ከተሞችን መንደሮችንና፥ ግለሰቦችንም ጭምር ለተራ ዝርፊያ አጋለጠ። በሰሜን በደብረማርቆስ ተመድበው የነበሩት ሚስዮናውያን የመጀመሪያዎቹ ሰለባዎች ነበሩ። ንብረታቸውን ቢያጡም ጥቂት ከመንግሥት ወገን የሆኑ ተዋጊዎች ባደረጉላቸው እገዛ መሠረት ነፍሳቸው ተርፋ በጊዜ አዲስ አበባ ሊደርሱ ችለዋል።

በደቡብ በኩል በጌዴኦና በጉጂ ሕዝብ መካከል በቱቲቲ ጣቢያ ሲያገለግሉ የነበሩትና የሲዳማ ሚስዮናውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመመካከር ወደ ይርጋ ዓለም ተሰባሰቡ። ከምክክሩ በኋላ ሁለቱ በይርጋ ዓለም መቆየትን ሲመርጡ ስምንቱ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። የካቲት 5 ቀን 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባ ደርሰው በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ በሲዳማ ሊያቆያቸው የሚችለውን ምግብና መድኃኒት ይዘው ጥቂቶቹ ወደ ይርጋዓለም እንደገና ተመለሱ።

የኢትዮጵያ ጦር ከተበተነ በኋላ ሕግና ሥርዓት ጭራሹኑ ተፋለሰ። ይርጋ ዓለም ከነበሩቱ መካከል ሁለቱ ወደ ሶዶ ሄደው እዚያ ካሉት ሚስዮናውያን ጋር መቀላቀልን መረጡ። አንዱ የኖርዌይ ቀይ መስቀል ማኅበርን ተጠግቶ በኬንያ በኩል ወጣ። ባለቤቱና ህጻን ልጁ አዲስ አበባ

መሆናቸው ያስጨነቀው ወጣቱ ክሊፍ ሚሼል እጮኛውን ለማግኘት ከሚናፍቀው ከቶም ዴቨር ጋር ሆነው ወደ አዲስ አበባ ለመጓዝ በመወሰናቸው ሚያዝያ 29 ቀን ከይርጋዓለም ተነሱ። አብረዋቸውም ሃያ ያህል መንገደኛ ነበሩ። የከሴ በረሐን ሲያቋርጡ ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም. ሽፍቶች ገደሏቸው።



ቶም ዴቨር

ምንጭ ፡ Cords of Love

ወጣቱ ክሊፍ ሚሼል በቆረቆረው በቱቲቲ ጣቢያ ዙሪያ ዛሬ በመቶ የሚቆጠሩ የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አብበዋል።

በጨንቻየነበሩትሚስዮናውያንን የአካባቢው ሹ ሞች በሆነው ባልሆነውሲያ ስቸግሯቸው ሰነበቱ። የነጭ ጥላቻ እንደገና ያመረቀዘበት ጊዜ በመሆኑ ሚ/ር ጆን ትሬዊን የተባሉትን ሚስዮናዊ ሁለት ጊዜ አስረው ከፈቷቸው በኋላ በሦስተኛው ላይ በራሳቸው የውሻ ሰንሰለት ጠፍረው አሰሯቸው። ሹሞቹ በውሻ ሰንሰለት ማሠራቸው የስድብ መልእክት ለማስተላለፍ እንጂ ታሳሪው አደጋ ያመጣብናል ከሚል ስጋት አልነበረም። በመጨረሻም በሁለት ዙር ዝርፊያ ንብረታቸውን አስረክበው ሰኔ 7 ቀን 1928 ዓ.ም. ሶዶ መጥተው ከሌሎች ሚስዮናውያን ጋር ተቀላቀሉ።

በማረቆ ያሉት ሁለት ልጃገረድ ሚስዮናውያን በእግዚአብሔርና በአቶ ደምበል እርዳታ እንዴት እንደተረፉ በቀዳሚው ምዕራፍ ውስጥ የአቶ ደምበል መጠመቅ ሲገለጽ እግረ መንገዱን ተጠቅሷል። አቶ ደምበል ሁለቱን ሴቶችን ወደ አዲስ አበባ ይዘው ሲጓዙ የአካባቢውን የጎሳ መሪዎችን ጦር ለርዳታ በማስተባበር አልፎ አልፎ የሚያጋጥማቸውንም አደጋ በመቋቋም ከግል አገልጋዮቻቸው ጋር ሆነው በኃይል እየጣሱ በግለፍ የማንነታቸውን ታላቅነት አስመስክረዋል።

በከምባታና ሃዲያ የነበሩት ሚስዮናውያን ሚስተር ካውዘርና ባለቤታቸው፥ ጆን ፊሊፕስና ባለቤታቸው እንዲሁም ዚላ ዎልሽ አንዳንዴም ሹማምንቱ እያስጠጓቸው፥ ሹማምንቱን መጠጋት አደጋ እንደሚስብ በሚያስቡበት ጊዜ ደግሞ በአማኞች ቤት በመሸሸግ አራት ወራት ያህል በዚያው አሳለፉ። በዚህ ወቅት ነበር የሚስዮናውያኑ የቅርብ ሰው የነበሩት አቶ ሙሉነህ ወዳጆቻቸውን ከወረበሎች ሲከላከሉ ሕይወታቸውን የሰውት።

ከአራት ወራት መናወጥ በኋላ የሆሳዕና አገረ ገዥ አንጻራዊ ሰላም ሊያሰፍኑ ስለቻሉ ሚስዮናውያኑን ከተሸሸጉበት የገጠር ቀበሌዎች ልከው አስመጧቸው። አንድ ወር በሆሳዕና ከተቀመጡ በኋላ የወላይታ አገረ ገዥ አጃቢ ወታደሮችን ልከው በመስከረም 27 ቀን 1929 ዓ.ም. ወደ ሶዶ አስመጧቸው።

የላምቡዳ ሚስዮናውያን ወደ ሶዶ በተወሰዱበት ቀን አብረዋቸው ከተጓዙት የሃዲያ ሰዎች መካከል አባ ጎሌ ኑነሞ፥ አቶ ሽጉጤ እና አቶ ረጣቦ ይገኙበታል። አባጎሌ በአፍላው ጦርነት ጊዜ (በዚያን ወቅት ገና ክርስትናን አልተቀበሉም ነበር) የሚስዮናውያኑን ሕይወት ለማትረፍ ከተረባረቡት ባለውለታዎች አንዱ ናቸው።አባጎሌ ይበልጥ የሚታወቁት ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ባርያ ፈንጋይ እና ባለውቃቢ በመሆናቸውና አንዳንዴም ሲመቻቸው በቀማኛነታቸው ነበር። ቁመታቸው ግዙፍ፥ ድምጻቸው ነጎድጓዳማ፥ ጉልበታቸው ከጤነኛው ሰው መጠን ያለፈ ስለነበር ይፈራሉ። እንዲህ ያለው ሰው እነዚያን ባይተዋር ፈረንጆች ለማገልገል (ያውም ወንጌልን ሳይቀበል) ራሱን መስጠቱ መቼም የሚያስገርም ነው፤ በእንበሳ አፍ ሥጋ በአደራ የማስቀመጥ ያህል ነውና።

ሌላው የሚያስገርመው ምሥጢር አባጎሌ ከዝነኛ ታዋቂ ተዋጊዎች አንዱ ሆነው የሌሎችን ሕይወት ከምትና ከምርኮ ሲያድኑ ለካስ የእሳቸው ሚስትና አንዱ ልጃቸው በእርስ በርሱ ግጭት ሳቢያ ተማርከው ወደ ወላይታ ተግዘው ኖሯል። ስለዚህም ምርኮኞቹን ለማስለቀቅ ወደ ወላይታ ሲሄዱ ከሚስዮናውያኑ ጋር መነዳኘትን መረጡ። አቶ ሽጉጤ በጦርነቱ ወቅት ቤታቸው ተቃጥሎ ከብቶቻቸውም ተዘርፈው ስለነበር ወደኋላ

የሚጎትታቸው አልነበረምና አቶ ረጠቦን ጨምረው እነዚህ ሦስቱ የአገሬው ሰዎች ሚስዮናውያኑን አጅበው ወደ መላይታ ሄዱ።



አባጎሌና ቤተሰባቸው በጉልምስና ጊዜ

ምንጭ ፡Cords of Love

እግዚአብሔር አምላክ አሠራሩ እጅግ ግሩምና ድንቅ ስለሆነ ሚስታቸውንና ልጃቸውን ለማስፈታት ደጅ የሚጠኑት አባ ጎሌ ትርፍ ሰዓታቸውንና አዳራቸውን አቶና ሚስዮን ጣቢያ አደረጉ። የሚስዮኑ ዘበኛ አቶ ዳርጌ ከጥበቃ ሥራቸው ይልቅ ለወንጌል ሥራ ልባቸው የተቀጣጠለ ስለነበር ለሚያገኙት ሁሉ ስለክርስቶስ ግዳን ሳይነግሩ አይለቁትም። አባጎሌ ትተውት የመጡት ቤትና ንብረት ስላሳሰባቸው ወደ አገራቸው ለመመለስ ተቻኩለው የምርኮ ማስለቀቂያ ዋጋ (ቤዛ) ከፍለው የመጨረሻዋን ቀን ይጠባበቁ ነበር። በዚህን ወቅት ነው ሌሊት በተኙበት እግዚአብሔር በራእይ የተገናኛቸው። በማለዳው ተነስተው ወደ ክርስቶስ እምነት መመለሳቸውን በግልጽ አወጁ። ወደ አገራቸው ሲመለሱ ፍጹም ሌላ ሰው ሆነው ነበር። "ወንሸጁው" አባጎሌ መላይታ ቀርቶ የእግዚአብሔርን ሥራ ቀንበር ተሸካሚው አባጎሌ ዱባንቾ ደረሰ። በኋላ ቀስ በቀስ እንደምናየው የከምባታና የሃዲያ የወንጌል ሥራ መልክ የተለወጠው ከእሳቸው ሕይወት መለወጥ ጋር ለመሆኑ ፍሬው ምስክር ነው። በአፍላው የኢጣሊያ ወረራ ወቅት በመከራው መሐል የላምቡዳን ሚስዮኖች አጅበው የሄዱት አቶ ሽጉጤ እና አቶ ረጠቦም የተጠመቁት በዚሁ አጋጣሚ በሶዶ ነበር። የአቶ ሰብሮ ስም ለጥቂት ጊዜ መሰወር አዲስ አበባ ከሚ/ር ዳፍ ቤት በሠራተኝነት

በመኖራቸው ምክንያት ነበር። አቶ ሰብሮ የተጠመቁትም በሐምሌ ወር 1928 እዚያው አዲስ አበባ በነበሩት ጊዜ ነው።

25. የአገልግሎት ርክክብ

በ1929 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ በደቡብ ኢትዮጵያ የነበሩት ሚስዮናውያን በሶዶ፤ በሰሜን የነበሩቱ ደግሞ በአዲስ አበባ ተከማቹ። ታህሳስ 11 ቀን 1929 ዓ.ም. ወላይታ ሶዶ በጣሊያኖች እጅ ወደቀች። ከየካቲት ወር አንስቶ የሶዶ ሚስዮናውያን ቀስ በቀስ ወደ አዲስ አበባ መጓጓዝ ጀመሩ።ሚያዝያ 9 ቀን 1929 ዓ.ም. የመጨረሻዎቹ ተጓጉች አዲስ አበባ ደረሱ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ሰፊ ምድር የተዘራችው የሰናፍጭ ቅንጣት የራሷን መልክ ይዛ ታየች። አዲሲቷ ቤተ ክርስቲያንና የበኩር ልጆችዋ የጨለማው ገዢ በሠለጠነበት ምድር ያቀጣጠሉት ችቦ ደማቅ ብርሃን መስጠት ጀመረ። በመጀመሪያ ለክርስቶስ የተሰጠው ሕይወታቸው፥ ቀጥሎም ትምህርታቸውና ኑሮአቸው ሚስዮን ሳያጠላበት ብቻውን እንዲቆም ጊዜው ግድ አለ።

ለዘጠኝ ዓመታት ያህል አዲስ አበባን ጨምሮ በአስራ አምስት ጣቢያዎች ሰፍረው የተለያዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የሰጡት የኤስ.አይ.ኤም. ሚስዮናውያን ብዛት ዘጠና ሁለት ያህል ነበር። በወንጌል አገልግሎታቸው ክርስትናን ተቀብለው የጥምቀት ስርዓት ከፈጸሙ አማኞች ብዛት ጋር ሲነጻጸር ምናልባት ንጻሬው አንድ ሚስዮናዊ ለአንድ የወንጌል አማኝ ያህል ነበር።

ከሞላ ጎደል የቤተክርስቲያን ቅርጽ የሚታይባቸው አውራጃዎች ደግሞ ወላይታ፥ ሲዳማ ፥ ከምባታና ሃዲያ ብቻ ነበሩ።

በበረሃ በወንበዴዎች እጅ ከተገደሉት ሚ/ር ክሊፍ ሚሸል ሚ/ር ቶም ዴቨር በስተቀር ነሐሴ 15 ቀን 1929 ዓ.ም. ሁሉም ሚስዮናውያን ኢትዮጵያን ለቀው ወጡ። የሚ/ር ክሊፍ ሚሸልና ሚ/ር ቶም ዴቨር

የሰማእትነት ደም ግን እንደ አቤል ደም እየጮኸ ቢዘገይም እንኳን በመቶዎች የሚቆጠሩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን አፍርቷል።

ሚስዮናዊያኑ በጦርነቱ ዋዜማ፥ በጦርነቱ ጊዜና በአርበኝነት ተጋድሎው ወቅት የነበረውን የሰላም መደፍረስ ቢያጤኑትም እንኳን አዲሲቱን ቤተ ክርስቲያን ወዲያ ጥለው ወደ ትውልድ አገራቸው ወይንም የሰላም ዋስትና ሊያገኙ ወደሚችሉበት ሌላ ቦታ ለመሸሽ ያለመፍጠናቸው ለአገልግሎታቸው ያላቸውን መሰጠት ያስረዳል።

የእነዚያን ፋና ወጊዎች መልካም አገልግሎት መተረኩ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ ስለሚስዮናውያን ያለውን በአብዛኛው አሉታዊ የሆነ አመለካከት ሚዛን እንዲጠብቅ ያደርገዋል። እኒያ የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መልእክተኞች ይህኛው ትውልድ በቅርብም በሩቅም ከሚያውቃቸውና የየራሳቸውን " ትንንሽ አሜሪካና አውሮጳ " ሰርተው በመካከሉ ሳይሆን እንደነረቤት ብቻ ከሚኖሩት ዘመንኛ ሚስዮናውያን በጣሙን የተለዩ ናቸው። ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ምሑር ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚገኝ አንድ ዩኒቨርስቲ ባቀረቡትና በዚህ ዙሪያ ባጠነጠነው የጥናት ወረቀታቸው ላይ ይህንን የብዙዎችን አመለካከት እንደሚከተለው ተጋርተዋል።

> ቀዳሚዎቹ ሚስዮናውያን ከጣሊያን ወረራ በኋላ አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ በኃይል ተገደዱ። እነዚያ ሚስዮናውያን በዚህ ዘመን ከምናውቃቸው ሚስዮናውያን በብዙ የተለዩ ናቸው። ከዘመነኞቹ አንዳንዶቹ መክራ እንደ አሳት በነደደ ጊዜ አገሪቱንና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እርግፍ አርገው ትተው ለመሄድ እንዲያመቻቸው ለጉዞ በተሰናዳ ሻንጣ ውስጥ ራሳቸውን ቆልፈው የሚኖሩ ይመስላሉ። ይህን ደግሞ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወድቆ ሥልጣኑን ኮሚኒስቶች በያዙ ጊዜ አይተነዋል፥ አብዛኛዎቹ ሚስዮናውያን አገር ጥለው የነጎዱት መንግሥት ይህ ነው የሚባል ግፈት ሳያደርግባቸው ነውና።[3]

የቀድሞዎቹ ሚስዮናውያን ከአገር እንዲለቁ በተገደዱበት ወቅት ምንም እንኳን ጽኑ የወንጌል ፍቅር የነበራቸው ቢሆንም ከመውጣታቸው በፊት ግን በየትኛውም ክፍለ አገር ወይም አውራጃ የሚሰዮን ጣቢያ እንጂ ቤተ ክርስቲያን አላነጹም ነበር። እርግጥ ነው በሲዳማና በወላይታ አነስተኛ

የግር ቤቶችን ለጸሎት ቤትነት እንዲያገለግሉ አማኞቹ ራሳቸው ሠርተው ነበር።

የሆስፒታሎች፥ የትምህርት ቤቶች፥ የመናሪያ ቤቶች ሕንፃዎች ግን በጥሩ ሁኔታ ታንጸው ነበር። ሚስዮናዊያኑ አገር ለቅቀው እንዲወጡ በታዘዘበት ጊዜ ጣሊያኖች ለመረሷቸው የሆስፒታል እና የት/ቤት ተቋሞች 18,870 የእንግሊዝ ፓውንድ የሚገመት ገንዘብ ለኤስ.አይ.ኤም .የሚስዮን ድርጅት ካሣ ከፍለዋል። ቤተ ክርስቲያን ግን ቋሚ ቅርስ እንዳልነበራት ተመልክተናል። በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጥኚዎች አነጋገር ምናልባት ቤተክርስቲያን የተወለደችው ሳይሆን የተቋቋመችው ሚስዮኑ ከለቀቀ በኋላ ነው የሚሉት ከዚህ በመነሣት ነው። እውነተኛዋ ኩላዊት ቤተ ክርስቲያን ግን ሕንፃው ሳይሆን የአማኞች ስብስብ ስለሆነ ከሕንጻው ባሻገር ያለውን የክርስቶስን መሠረት ማየቱ መልካም ነው። በዚያን ወቅት በሚስዮናውያን እግር ተተክቶ ቤተ ክርስቲያኒቷን ለመምራት ብቃት ያለው እና " እገሌ " ተብሎ የሚጠቀስ ሰው ያለ አይመስልም ነበር። ሌላው ቢቀር የኢጣሊያ የወረራ ዝግጅት ወሬ መናፈስ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሚስዮናዊያኑ ከአገር መውጣት ባለው የሁለት ዓመት ጊዜ እንኳን በከፊል ለተደራጁት ቤተ ክርስቲያናት የአገሬውን ተወላጅ ሽማግሌዎችን አስመርጠው አመራርንና፥ አስተዳደርን እንዲለማመዱ አለማድረጋቸው ሚስዮናዊያኑ በአገር ሰው ላይ የነበራቸውን የብቃት ማነስ ጥርጥር የሚያመለክት እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን አስተያየት ይሰጣሉ። ለዚህ እውነት በቂ ማረጋገጫ የሚሆነው በወላይታ ኃላፊነቱን ለአቶ ብሩ ያስረከቡት ወላይታን ለቀው በወጡበት ዋዜማ ሲሆን ለከምባታና ሃዲያ ቤተክርስቲያን ደግሞ ሽማግሌዎችን የሰየሙት ከላምቡዳ ከለቀቁ በኋላ አዲስ አበባ ተከትለዋቸው ለሄዱት ሠራተኞቻቸው ነበር። ይህም ሁኔታ እንደሚከተለው ተገልጿል፤

> (ከመሸ በኋላ) በሚስዮናውያኑ የመጨረሻ ሰዓት ላይ ሽማግሌዎች መመረጣቸው የሚያመለክተው አመራሩን (እስከዚያ ሰዓት ድረስ) በቁጥጥራቸው ሥር ማድረጋቸውንና የአገሬው ተወላጆች ሕዝባቸውን እንዲያገለግሉ ራእይና ስልት ያለመቀየሳቸውን ነው። ይኸ አሠራር ኋላም (ከጣሊያን ወረራ በኋላ) በነበሩት ሚስዮናውያን ዘንድ ቀጥሎ የብሔራዊ ቤተክርስቲያንን የአመራር አቅም አደጋ ላይ ጥሎት ነበር። ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያንን ስለማነጽ ሚስዮኑ ብዙ

ያወራል። ነገር ግን ራሷን እንድትችልና ራሷን እንድታስተዳድር ከንግግር ያለፈ ተጨባጭ ነገር አልታየም።[4]

በጅግሬ ላይ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ይህንን የመሰሉ ፈታኝ አደጋዎች ገና በለጋነቷ ቢያጋጥሟትም በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምሪትና ጥበቃ ምክንያት ሚስዮናዊያን ከአገር ከወጡ በኋላም "ባልተማሩና በሰው ዓይን ፊት በተናቁ ተራ ሰዎች" ህያው አምላክ ዘላለማዊ የማዳን ሥራውን በሙላት ፈጸመ። በመከራ የተፈተኑ እና እንደ ወርቅ የነጠሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ተነስተው የተቀጣጠለውን የወንጌል ችቦ ይዘው የምሥራቹን ቃል በማወጅ ለተተኪው ትውልድም በታማኝነት ሊያቀብሉ ችለዋል።

26. የኢጣሊያ የሃይማኖት ፖሊሲ

ወራሪው ጦር ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ግማሥት ጀምሮ የሩሽስታዊ አገዛዝ መርሑን በገሃድ ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ። አዲስ ያስገበረውን የምሥራቅ አፍሪቃ ግዛት በሙሉ "አፍሪካ ኦሪያንታሌ ኢታሊያና " ሲል በቋንቋው ሰየመው። የጥንቱ የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ተሸሮ ከኢጣሊያ ሶማሌላንድ ጋር ተቀላቀለ። አዳዲስ ክልሎችም ተፈጠሩ። አከላለላቸው የአገዛዛቸውን ፖሊሲ በይበልጥ ይፋ ያደረገ ነበር። የሚከተለው የታሪክ እማኝነት ለዚህ ጉዳይ በማስረጃነት ይጠቀሳል!

> ከ1928 -1933 ዓ.ም የወረራ ዘመን ፋሹቶች ከፋፍለህ ግዛ በሚለው አሠራር የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ለማጠናከር በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎችና ማኅበረሰቦች ዘንድ በሥፍራ በሥራ፥ በብሔረሰብ፥ በማኅበራዊ ጉዳይ፥ በቋንቋ፥ በሃይማኖት፥ በሥልጣን፥ በመሬትና በዜግነት ጥያቄዎች አንዱን ክፍል የሚያጠቃ ሌላውን ደግሞ የሚጠቅም መንትያ ፖሊሲ መሠረቱ።[5]

ከዚህ በመነሣትም ትግራይንና ኤርትራን የሚያጠቃልለውን የኤርትራ ክልል! ጎንደር፥ ጎጃም ወሎ እና ሰሜን ሸዋን በአንድነት

"የአማራ" ክልል፥ የደቡብና የደቡብ ምዕራብ ክፍለ አገራትን ደግሞ "የጋላና የሲዳማ" ክልል፤ የመናገሻ ከተማዋን ዙሪያ "አዲስ አበባ፤" አጋዴንና የሶማሊያ ቅኝ ግዛታቸውን "የሶማሊያ ክልል"፤ ሐረርጌ እና አርሲ ክፍላተ አገራትን ደግሞ "የሐረር ክልል" ብለው አዋቀሯቸው።

የክልሎቹ ዋና ማእከላት ደግሞ አሥመራ፥ ጎንደር፥ ጂማ፥ ሐረር፥ አዲስ አበባ፡ሞቃዲሾ እንዲሆኑ ተወሰነ።

በሃይማኖት አንጻር የካቶሊካዊቷን የሮማ ቤተ ክርስቲያንን ሕዝቡ በይፋ እንዲቀበል መገፋፋታቸው እና ሃይማኖቱንም ለተቀበለ ሰው ልዩ ድርጎ መስጠታቸው እርግጥ ሆኖ ታዩ። ፋሽስቶች ለፕሮቴስታንቶች የነበራቸው ጥላቻ ሃይማኖታዊ ቅንዓት ብቻ ሳይሆን " ዓለም አቀፍ ጠላታችን " ከሚሏቸው ከአሜሪካና ከእንግሊዝ ጥቅሞች ጋር ስለሚያያይዙት ጭምር ነበር።

" በቀንበራችን ሥር ወድቃለች " ለሚሏት ለኢትዮጵያ ፕሮቴስታንቶች ግን ጥላቻቸው ከዚህም አለፍ ይላል። ተራ በተራ በአጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን፤

የመጀመሪያው ጥላቻ የመነጨው ጣሊያኖች የግዕዝ ፊደላትን በላቲን ለመለወጥ ካላቸው ጽኑ ምኞት የተነሣ ነበር። በወቅቱ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ተተርጉሞ በስርጭት ላይ እንደነበረና ቀደም ባሉት ገጾች እንደተገለጸው በጎፋ፥ በወላይታ፥ በሃዲያ፥ በአሮሞ ቋንቋዎች የተተረጎሙት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች የተጠቀመበት ቋንቋ ደግሞ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀመበትን የግዕዝ ፊደል ነበር።

ሚስዮኖች እያሉም ሆነ ከሄዱ በኋላ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ዘንድ የክርስትና እምነትና የመሠረተ ትምህርት እውቀት ወይንም ማንበብና መጻፍ ተጓዳኝ ነበሩ። በሌላ አገላለጽ በወንጌል ያመነ ሁሉ ራሱን በመንፈሳዊ ምግብ ለመመገብ ፊደል ቆጥሮ መጽሐፍ ቅዱስን ያነባል። አንድ ሰው አመነ ማለት ንባብ ቻለ ማለትም ነው። ያ ሰው ታዲያ የአማርኛን ንባብ ከቻለ የጣሊያኖች ዋና ጠላት ሆኖ ይቆጠራል፤ ይሰደዳል፥ ይታሠራል ከአካባቢውም ይባረራል።

በሁለተኛ ደረጃ ጣሊያኖች የወንጌል አማኞችን የጠሉበት ምክንያት አማኞቹ ስለአገራቸውና ስለ ሕዝባቸው ሰላምና እረፍት በስደት ላይ ለነበሩትም ንጉሠ ነገሥት ሁልጊዜ የሚጸልዩት ጸሎት ለጣሊያኖች በተሳሳተ ትርጓሜ ግለትም ለንጉሣቸው ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን እንደገና መመለስ አድማ ያደርጋሉ (ይቀሰቅሳሉ) ተብሎ ስለተወራባቸው ነበር።[6]

የመከራው ክብደት የፀና ቢሆንም የወንጌሉን ብርሃን ሊያጠፋው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተመዘገበው በስተቀር ከየትኛውም ታሪክ ጋር ተነፃፅር ሊወዳደር የማይችል መነቃቃት የደቡብ ኢትዮጵያን ገጠሮች ሁሉ አዳረሰ። አቶ ግንኝ የተባሉ የቀድሞ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አማኝ እንደሚሉት " የተጠማ እንስሳ ወደ ውኃ እንደሚገሰግስ ሰዎች የባእድ አምልኮአቸውን ወደኋላ እየጣሉ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ።"[7]

ቢቻል የመከራው ጎርፍ በክርስቶስ ያመኑትን አንድም ሳያስቀር ጠራርጎ እንዲወስድ ታስቦ የተዘጋጀ ነበር። ነገር ግን እንደብረት የጠነከሩ እንደወርቅ የነጠሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ወለደ። በሲዳማ አቶ ገንሜ፥ በወላይታ አስቀድሞም አቶ ብሩ፥ ኋላም አቶ ዋንዳሮ፥በከምባታና ሃዲያ በመጀመሪያ አቶ ሽጉጤ ቀጥሎም አባጎሌ የሚያህሉ የወንጌል አርበኞች በሞገስና በጸጋ ተቀብተውና ጎልተው ሊወጡ ችለዋል።

የወላይታ ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ አማኞች የወንጌል ሥርጭቱን ስልት በድግሚት ፍንዳታ ይመስሉታል። ለዘላለም አይነኬ ሆኖ በቆየው ቋጥኝ ስር ተቀብሮ ሲፈነዳ ፍንጣሪው አካባቢውን እንደሚያለብስ ድምጹም ምድርን እንደሚያናውጥ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል በኃይልና በመንፈስ በአያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ተገለጠ! ዝናውም መላ ደቡብን ሞላ።

በወላይታ ሚስዮናውያኑ ከአገር ከመውጣታቸው አስቀድሞ የነበሩት ተጠማቂ አማኞች ቁጥር አርባ ስምንት ብቻ ነበር። ከዚያም ስድሳ ዘጠኝ ቀጥሎም ሰባ ሦስት ደረሰ። በመከራው ወቅት ግን የተጠመቁት ቁጥር አስራ አምስት ሺህ ያልተጠመቁትና በወንጌል አምነው በቋሚ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ሥነ ስርዓት የሚሳተፉት ብዛት በአስር ሺህ የሚገመት ነበር። ሚስዮን በነበረበት ወቅት የተተከለችው " ጸሎት ቤት " አንድ ብቻ ነበረች

በመከራው ዘመን ያሉት " ቤተ ክርስቲያናት " ግን ሁለት መቶ ያህል ደርሰው ነበር። በከምባታና ሃዲያ የአማኞች ቁጥር ሚስዮን ሳይለቅ ከሃያ አምስት አይበልጥም ነበር። በወረራው ዘመን የምእመናን ቁጥር አስር ሺህ፥የቤተ ክርስቲያናት ብዛት ደግሞ አንድ መቶ ያህል ደርሶ ነበር። ታዲያ እኒህን ሁሉ ወደ ክርስቶስ መንግሥት ለመመለስ የተከፈለው ዋጋ ቀላል አልነበረም። አቶ ብርሃኑ ደረሰ ሥፍራው ድረስ በመሄድ ባጠኑት ጥናት እንዳመለከቱት በወላይታ ብቻ በወረራው ዘመን ከታሰሩት አምሳ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል አርባ ዘጠኙ መሪዎች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ጅራፍ ተገርፈዋል። አንዱ የቤተክርስቲያን መሪ አምስት መቶ ጅራፍ ተገርፈዋል።[8] ግርፋቱ ባስከተለው ሕመምና በእስር ቤት ውስጥ በነበረው መተፋፈግ የተነሣም ሕይወታቸው ያለፈ አማኞችም ነበሩ። ሁለት ሌሎች አማኞች ደግሞ በኢጣሊያኖች ትዕዛዝ ታፍነው ተወስደው የደረሱበት ሳይታወቅ ቀርቷል።

የኢጣሊያ ፋሽስቶች የሃይማኖት ፖሊሲ ሁለተኛው ስልት ከመጀመሪያውና ቀጥተኛ ከሆነው ስደትና ተቃውሞ ይልቅ ይበልጥ የረቀቀና አደገኛ የሚባል ዓይነት ነበር፤ አንድ የታሪክ ምሁር እንዲህ ይገልጹታል፤

> በፋሽስቶች አመለካከትና ግንዛቤ በምኒልክ ፖሊሲ መሠረት የኢትዮጵያን በሀውርታዊ መንግሥትና ጎብረተሰብ በበላይነት የሚገዛው ብሎም በአገሩ በኢጣሊያ ኮሎኒያዊ ጥቅምና ጸጥታ አደገኛው ጠላት የአማራ ማኅበረሰብ ነው። ፋሽስት ባለሥልጣናች ከዚህ አቋማቸው በመነሣት በመጀመሪያ ዓመታት በተሰጣቸው የፖሊሲ መመሪያ በአማራ ማኅበረሰብና በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ መንግሥታዊ የጥቃት እጅ አነሱ። በዚህ ረገድ ለምሳሌ ከ600,000 እስከ 800,000 የሚገመቱ አማርኛ የሚናገሩ ነዋሪዎች ከሐረር እና ከሲዳማ አስተዳደር ክልሎች እንዲባረሩ....እርምጃዎችን ወሰዱ።[9]

የተንኮል እቅዳቸውን ለማስፈጸም እና የአማራን ብሔረሰብና የአርቶዶክስን ዕምነት "የበላይነትን" ለመሸርሸር እንደ መሣሪያ የተጠቀሙባቸው ሙስሊም ኢትዮጵያውያንና የእስልምና ሃይማኖትን ነበር። ስለዚህም ሙስሊሞችን በጥቅም ለመሳብ ሰፊ የሥራ ዕድልን በመፍጠር የበርካታ ሺህ ሊሬ ተጠቃሚ አድርገዋቸዋል።[10]

ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በሁሉም ጉዳይ የመጀመሪያ ዕድል ይሰጡ ነበር። በዚህ ነገር በዲፕሎማሲና በንግድ ዓለም አቀፍ ድጋፍ ለማግኘት የኢጣሊያ ፋሽስት መሪ ሙሶሊኒ ለዓለም በአጠቃላይ ለመካከለኛው ምሥራቅ የእስላሙ ዓለም በተለይ ራሱን ለኢትዮጵያ የእስላም ሕዝቦች ጠበቃና ሐዋርያ አድርጎ ያቀርብ ነበር።[11]

ሙሶሊኒ በዚህ ብቻ ሳያበቃ በሐረር እና በጂግ ከተሞች ሁለት እስላማዊ ዩኒቨርስቲዎች የማቋቋም ሐሳብ ከመንደፉም በተጨማሪ የኢትዮጵያ እስላሞች ወደ መካና መዲና በብዛት እንዲሄዱ መንገዱን ጠረገላቸው። የአገራቸው ነጻነት የሚያሳስባቸውን ሙስሊሞች ትኩረት ለመሳብም ፋሽስቶች በኢትዮጵያ በቆዩባቸው አምስት አመታት ውስጥ

"በትንሹ አምላ አዳዲስ የድንጊያ መስጊዶች እንደተገነቡ፥ አሥራ ስድስት አሮጌ የድንጋይ መስጊዶችን እንደ ታደሱና በየአካባቢው ሁሉ ከእንጨትና ከጭቃ ብዙ መስጊዶችን እንደተሠሩ ተረጋግጧል።[12]

የኢጣሊያን ፋሽስት አገዛዝ ቤተ ክርስቲያናትን እያፈራረሰ፥ በፍርስራሹም ፋርና እየጋገረ መስጊዶችን ማነጹ፥ ክርስቲያኖችን እያሳደደ ሙስሊሞችን የጥቅሙ ተካፋይ ማድረጉ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የመኖር ልማድ ባይለዝብና የወንድማማችነቱ ፍቅር ባያይል ኖሮ በሕዝባችንና በታሪካችን ውስጥ በቀላሉ የማይነቀል መርዝ ትቶ ባለፈ ነበር።

ጣሊያኖች የፈጸሙትን ረቂቅ ደባ ስንመረምር ታሪክ በጊዜና በሥፍራ በሁኔታም ራሱን መድገሙን እናጤናለን። ለዚህ ምስክር የሚሆነን በ1870 ዓ.ም. ንጉሥ ምኒልክና አጼ ዮሐንስ ቦሩ ሜዳ ላይ ተገናኝተው ከተዋህዶ አርቶዶክስ ሃይማኖት ሌላ ሌሎች ሃይማኖቶች በአገሪቱ ውስጥ እንዳይገኙ የፖለቲካ ውሳኔ ማድረጋቸው ነው። በዚህም ምክንያት እስልምናንና የወንጌላዊ እምነትን የሚቃወሙ ግብጻዊ አቡኖች በርከት ብለው እንዲገቡ አደረጉ። በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በጦርና በሃይማኖት ሹማምንት መሪነት ወታደሮችን ከሕዝብ ጋር እያሰፈሩ በአገር አቀፍ ዘመቻ ብዙ የአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናትን አሳነጹ። ቀድሞ ክርስቲያን ያልነበሩትን ባላባቶች ክርስትና አነሱ።

ለምሳሌ፤ በወሎ ከጠንካራዎቹ መሣፍንት መካከል መሐመድ ዓሊን "ሚካኤል" አሰኝተው አጼ ዮሐንስ ክርስትና ሲያነሷቸው፥ ንጉሥ ምኒልክ ደግሞ የቀድሞ ደመኛቸው የነበሩትን አባ ዋጠው ሊበንን ኃይለማርያም አሰኝተው የክርስትና አባት ሆኗቸው። ሁለቱ ነገሥታት ብቻ ሳይሆኑ ሌላውም ሹም፥ መስፍንና ባላባት የነገሥታቱን ፈለግ ተከትሎ በውድም በግድም ብዙዎችን ወደ አርቶዶክሳዊ እምነት መለሰ። ቤተክርስቲያናትን በዘመቻ መልክ በየጭቃሹሙ ደጅ አሳነጹ። በዚህ ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች እንዳመለከቱት ዳግማዊ ምኒልክ ባወጡት የቤተክርስቲያን ተከላ አዋጅ መሠረት በመላ አገሪቱ የተሠሩት ቤተ ክርስቲያናት አንድ ሺህ ሁለት መቶ ያህል ነበሩ። የንጉሥ አዋጅ ነውና በዘመቻው ሙስሊሞችና ልማዳዊ እምነትን የሚከተሉ ሁሉ ተሳታፊ ነበሩ። አዋጁ እንደሚከተለው ይነበባል፤

> ስማ ያገሬ ሰው፤ ጌታችን፥ ኃይላችን፥ ረዳታችን፥ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገራችን፥ ለመንግስታችን ሰላምና እረፍት ሰጥቶን ይህን ያህል ቀን አኖረን አስገዛን። እኛም ይህን ሁሉ አስበን መርዳት ይገባናል። እኔ ራሴ የከተማዬን ዘበኞች ይዤ ከከተማ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት እሰራለሁ አድሳለሁ። ሹማምንቱም ባለጉልትም በያጥቢያህ ያለው መቅደስ ቤተ ክርስቲያኑ የፈረሰውን በመቃረቢያ ለተቀመጠው ታቦት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ሥራ። ወታደርም ባላገርም ጉልበት ያለህ እርዳ። አናጢም ገምቢም በያለህበት ለቤተ ክርስቲያን ሥራ እርዳ። የሃይማኖት መሰረቱ የክርስቲያን ምልክቱ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ነው። ለጉልበትህ ለገንዘብህ ሠሥተህ ቤተ ክርስቲያን አልሰራም ብለህ የመሰለትህ ሰው በሰማይ ይፈረድብሃል። በምድርም ሹመትህን ገንዘብህን ታጣለህ... 1889 ዓ.ም.[13]

ከዚህ በላይ የተነበበው አዋጅ በኢትዮጵያ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ትስስር ወይም ጋብቻ ምን ያህል "የጦፈ"እንደነበረ ጉልህ ማስረጃ ነው። ከጋብቻው የተወለደው አመለካከት ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ከአርቶዶክሳዊነት፤ አርቶዶክሳዊነትን ከኢትዮጵያዊነት የሚለያይ ድንበር ያለመኖሩን ለዘመናት ሲያስተጋባ ቆዬ[14] በሌላ አገላለጽ ከመንግሥትና ከቤተ ክርስቲያን ጋብቻ የተወለደው "የተበረዘ" አስተሳሰብ የአርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ያልሆነውን ሁሉ የዜግነት መብት የሚጋፋ ሆኖ

በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች ጎሊና ላይ ገዝፎ እንዲኖር ምክንያት ሆኗል።[15]

በዚህም መንስዔነት የኢጣሊያ ወራሪዎች በኦርቶዶክሳዊነት የወዛውን ኢትዮጵያዊነት ለማደብዘዝ በማቀድ ኦርቶዶክሶችን ፊት ነስተው፥ አብያተ ክርስቲያናትን በቦምብ አንድደውና መስጊዶችን በዘመቻ ሲያሠሩ ለወንጌል ሩጫ የተሻለውን እንቅፋት አንስተው ሌላውን ጉቶ መትከላቸው እንደሆነ አልታያቸውም ነበር። ሊታያቸውም አይገባም። ትንታኔው ከወንጌል ስርጭት አንጻር ብቻ እንደሆነ ልብ ይሏል።

27. በጊዜውም ያለጊዜውም

"...ኃይልህ ብዙ ሲሆን ጠላቶች ዋሹብህ። (መዝ. 66፡3)

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ውጭ አገር ከተሰደዱ በኋላ በሰሜን በምሥራቅና፥ በደቡብ የጦር ግምባሮች የተሰለፈው ጦር የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማሚሻ እስከሚመስል ድረስ ዘመኑ በፈጠራቸው አዳዲስ መሣሪያዎች ተጨፍጭፎ የተረፈውም በዱር በገደሉ ተበታተነ። ጣሊያኖች አገሪቱን በተለያዩ የአስተዳደር ክልሎች አዋቅረው የተመኙትን የቅኝ ግዛት ሲሳይ ለማፈስ ሲቻኮሉ በአራቱም የአገሪቱ ማዕዘናት የተቀጣጠለው የአርበኞች ተጋድሎ እረፍት ነሣቸው።

እንዲያውም በ1928 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ አርበኞች አዲስ አበባን አጥቅተው ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ እስከ 1929 አጋማሽ ድረስ ጣሊያኖች ወደ ደቡብ እንደልባቸው እንዳይዘዋወሩ አገዳቸው። እስከዚህ ወቅት የነበረው የአርበኞች ተጋድሎ ፈራ ተባ፥ ያዝ ለቀቅ ያለና ጥንካሬውም የሳሳ ነበር።

ከየካቲት 12 ቀን 1929 በኋላ ግን ትግሉ የሞትና የሽረት ጉዳይ ሆነ። ምሬቱ የተባባሰበት ምክንያት እንዲህ ነው፤ በተጠቀሰው ቀን ፋሺስቶች በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (የአሁኑ 6 ኪሎ ዩኒቨርሲቲ) ግቢ

ውስጥ ለመኳንንቱ ግብዣ ለድሃው ምፅዋት አድርገው ነበር። ግብዣው የተደረገው የኔፕልስን ልዕልት ልደት ምክንያት በማድረግ ነበር።



አርበኛው ዙሪያዋን በሽቦ የታጠረችውን የአዲስ አበባ ከተማን ከሩቁ ሲመለከታት

ምንጭ ፡ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት



ማርሻል ግራዚያኒ የፋሽስት ኢጣሊያ
የጦር አዛዥ በኢትዮጵያ

ምንጭ ፡ Adiss Tribune

በፋሽስቶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ የነበራቸው ኢትዮጵያውያኑ ሞገስ አስገዶምና አብርሃ ደቦጭ የተባሉ ሁለት ወጣቶች በግራዚያኒ ላይ ቦምብ ጥለው አቆሰሉት። የፋሽስቶቹ ምላሽም እጅግ መራራ ሆነ። አዲስ አበባ በደም ጎርፍ ታጠበች። ያንን ወቅት ባህሩ ዘውዴ እንዲህ ይገልጹታል:-

> ... ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች እየተባሉ የሚታወቁት የፋሽስት ደቀመዛሙርት .... አዲስ አበባን ቄራ አደረጓት። የሰው ልጅ ጭንቅላት እንደ ዶሮ እየተቀነጠሰ ወደቀ፤ እርጉዝ ሴቶች በሳንጃ ተወጉ። ... የተማሩ ኢትዮጵያውያን ... በወረንጦ እየተለቀሙ ተረሸኑ። ይህ የፋሽስት ጭፍጨፋ በሌላ መልኩ በወራሪና ተወራሪ መካከል ያለውን ቅራኔ መካረር በማመልከት የፀረ ኢጣሊያ ተቃውሞውም ከመጀመሪያው ወደ ሁለተኛው ምዕራፍ ከመደበኛ ወይም ከፊል መደበኛ ጦርነት ወደ ሽምቅ ውጊያ መሸጋገሩን አረጋገጠ። ይህን ሁለተኛውን የተቃውሞ ምዕራፍ በተመለከተ ግለት የሚቻለው አንድ ዐቢይ ነገር ሀገር አቀፍ መሆኑ ነው።[13]



የኢትዮጵያ አርበኞች (1928 – 1933)

ምንጭ ፡ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ትጽ 2

ይህን አገር አቀፍ የአርበኞች ትግል ለማኮላሸት የፋሽስት አዝማችች ከፋ ጠቅላይ ግዛት ያሉትን አርበኞች የሚወጋ ግዙፍ ጦር በኩሉ በኩል አዘመቱ። ዓላማው በኩሉ እና በኮንታ ባሉት አርበኞች ላይ ጫና ፈጥሮ ወደ ጥምባሮ እንዲያፈገፍጉና በዚያም በተዘጋጀላቸው ወጥመድ ውስጥ እንዲወድቁ ለማድረግ ነበር። አርበኞቹ ግን በወጥመድ ሊወድቁለት ቀርቶ ከጠላት በላቀ ስልት ምሽጉን ሌሊት ሰብረው ወራሪውን ሠራዊት እንዳልነበረ አደረጉት። ሰላማዊው ሕዝብ ግን የፋሽስቶቹን የበቀል ጽዋ ጠጣ። መንደሮች ወደሙ፥ከብቶች ተዘረፉ። በሺህ የሚቆጠሩ የኩሉ ተወላጆች የአሞ ወንዝን ተሻግረው ወደ ጠምባሮ ተሰደዱ።

የኩሉ ሰዎች መከራና ስደት በወላይታ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተሰማ። በጊዜው በወላይታ ታላቁን መንፈሳዊ መነቃቃት የሚመሩት አቶ ብሩ ዱባለ የኩሉ ተወላጅ እንደመሆናቸው የወገኖቻቸው መፈናቀል እጅግ ጎዘን ሆነባቸው። ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር መክረው አቶ ኡምቦሊ እና አቶ ጎዳና ጉቱሉ የተባሉ ወንጌላውያንን መርጠው የኩሉ ሰዎች በስደት ወደ ከተሙበት ጠምባሮ ወረዳ ላኳቸው። ጠንባሮዎች ከጣሊያን ወረራ በፊት በከምባታና ሃዲያ አገልጋዮች አማካይነት ወንጌልን የሰሙ ቢሆንም እስከዚያ ሰዓት ድረስ ግን አንድም ሰው በክርስቶስ አመንኩ ያለ አልተገኘም ነበር።


የወላይታ ወንጌላውያን ቀዳሚው ተልእኮ የኩሉ ስደተኞችን ለማገልገል ቢሆንም የመጀመሪያው አማኝ የጠምባሮው ተወላጅ አቶ አልዳዳ ሆኑ። ከስደተኞቹ ደግሞ አቶ ሐታሳ ሃናቆ፥ አቶ ባለንጎ በኩ፥አቶ ጦና ጅጎ፥ አቶ ጋድና ጋጋ፥ አቶ ሃላሳ ጎቤ፥ አቶ ድልባቶ አያቶ፥አቶ አርጋው ስሜ፥ አቶ ዜማ ማኡ፥ እና ሌሎችም በክርስቶስ አመኑ። ጠንባሮን አልፈው ወደ ወላይታ ከተሰደዱትም መሐል አቶ ብበሶ እና አቶ አይዲቆ አይማሎ የተባሉት ሁለት ወንድማማቾችና ሌሎች ጥቂት ሰዎች ክርስትናን ተቀበሉ። ከእነዚህ ሌሳ ወደ ሃዲያ፥ ጎፋ፥ ጂማ፥ የተበተኑት ብዙዎች ነበሩ።

በአርበኞች ድል አድራጊነት ጦርነቱ በ1933ዓ.ም.ተፈጸመ። ስደተኞቹ ግን ወደ አገራቸው ሳይመለሱ እስከ 1938 ዓ.ም. ድረስ በጠምባሮ ቆዩ። በ1939 ዓ.ም. ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ተመለሱ። ከከምባታና ሃዲያ ሰዎች አቶ አልዳዳ አጤቦ እና አቶ ጡሚቦ የተባሉት

አገልጋዮች አብረዋቸው ተመለሱ። ስደተኞቹ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ በአንድ የተቀራረበ አካባቢ ሰባት ቤተ ክርስቲያናትን ተከሉ። የመጀመሪያዋ በአቶ ሐታሳ ደጅ የቆመችው ነበረች። እንደዚያ ባለው ጦርነት ወቅት በነፍሳቸው ተወራርደው በፈታቸው የሚያልፈውን አጋጣሚ ሁሉ ለወንጌል ስርጭት የተጠቀሙበት እኒያ የእግዚአብሔር ባሪያዎች እንዴት የተባረኩ ናቸው!?

ሁለተኛው አጋጠሚ

የኢትዮጵያ አርበኞች መፈናፈኛ ያሳጡት ወራሪው የጣሊያን ጦር በተቆጣጠራቸው ከተማዎችና አካባቢያቸው በሚኖረው ሕዝብ ላይ ሥነ ልቦናዊ ተጽእኖ ለማሳደር በ1932 ዓ.ም. ታላቅ ወታደራዊ ትርኢት በሶዶ ከተማ እንዲደረግ ወሰነ። ወታደራዊው ሰልፍ ሕዝቡ በሥራዊቱ ብዛት፥ በተኩሱ ጩኸት በጦር መሣሪያዎቹ ኃይል ተደናግሮም ሆነ ተገርሞ የጠላትን የበላይነት እንዲቀበል የታለመ ዕቅድ ነበር። ስለዚህም በወላይታ በጋሞ፥ በጎፋና ቁጫ ዙሪያ ባሉ አውራጃዎች ኗሪ የሆኑ ለአቅመ አዳም የደረሱ ሰዎች ሁሉ በግድም በውድም ሶዶ ከተማ ድረስ እንዲሰበሰቡ ተደረገ።




የፋሽስት ኢጣሊያን ወታደሮች የሰልፍ ትርኢት

ምንጭ ፡ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት

ይህ ወታደራዊ ሰልፍ ከመደረጉ ስድስት ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ግን አቶ ሕርባሮ እና አቶ ፈረንጄ የተባሉ አማኞች ከወላይታ ሑምቦ ወረዳ ተነሥተው ጋሞ አውራጃ ቆላ አቾሎ የሚባል አካባቢ ሄደው በቀን ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር። አቾሎ ብዙ ምርት የሚመረትበት አገር ስለሆነ በመከር ወቅት ሥራ ፍለጋ የሚሄዱ የወላይታ ሰዎች በርካታ ነበሩ አቶ ሕርባሮና አቶ ፈረንጄ የሄዱበትን የቀን ሥራ ሲሠሩ እየዋሉ ሌሊቱን የሚያሳልፉት ደጋ አቾሎ በሚባል አካባቢ ነው። ደጋ አቾሎ ለኑሮ ተስማሚ የሆነ አየር ያለበት ስለሆነ ከነዋሪው ብዛት የተነሣ መንደሩ ሞቅ ደመቅ ያለ ነው። እኒህ ሁለቱ አማኞች ሁልጊዜ ማታ ማታ ወንጌልን መመስከር ጀመሩ።ጥረታቸው ከንቱ አልቀረም ከሰሙት መካከል ስድስት ሰዎች በክርስቶስ አዳኝነት አመኑ። የመከር ጊዜ ሲያልቅ ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ተመለሱ።

በሚቀጥለው መከር ለመሄድ ሲዘጋጁ በጣሊያን ወረራ ምክንያት የአገሩ ጸጥታ ተናጋ። እኒያም ያመኑት ሰዎች ቅዱስ ቃሉን የሚያስተምራቸው መጋቢ ስላልነበራቸው ከማያምኑት የሚለዩት በጥቂቱ ነበር። ጣሊያኖች ሕዝቡ ወታደራዊ ሰልፉን እንዲመለከት በጠሩት ወቅት እኒያ ስድስቱ አማኞችና በሚስዮናውያን ስብከት በ1927ዓ.ም. ያመኑት አቶ ጌንቦ ወደ ሶዶ ከተማ ጉዞ ጀመሩ።



አቶ ጌንቦ ሶጋሞ ከጋሞ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ

ወላይታ ሶዶ ሳይደርሱ ቀኑ ስለመሸባቸው " የእግዚአብሔር እንግዶች ነን አሳድሩን " ብለው ወደ አንድ መንደር ጎራ አሉ። የመንደሯ ናሪዎች ሳያንገራግሩ አስተናገዷቸው። መጀመሪያ ወንጌል የመሰከሩላቸውንም ሲያጠያይቁ ወደ አቶ ሕርባሮ ቤት መሯቸው። መንፈሳዊ ነገር ተጠምተው ነበርና ሌሊቱን ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ሲጨዋወቱ አደሩ። እነ አቶ ጌንቦ ቀን ቀን ሲሆን ወደ ሶዶ ወጥተው የጣሊያንን ወታደራዊ ትርኢቱን ያያሉ ግታ ግታ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ይግራሉ፤ ሌሊቱን በጸሎት ያሳልፋሉ። በዚህ ሁኔታ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተቀጣጥለው ወደ ጋሞ ተመለሱ። ጣሊያኖች ተሸንፈው ከወጡ በኋላም የመጀመሪያይቱን የጋሞ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በዙሪ ቀበሌ ተከሉ።

በጋሞ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያዋ አጥቢያ ይህች የዙሪ ጸሎት ቤት ነች። ከዚህች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የበራው የወንጌል ብርሃን መላውን አቾሎ፥ ቦረዳ፥ ቦንኬ ላንቴንና ሌሎችንም የጋሞ ወረዳዎች ሁሉ አዳረሰ። በመቶ የሚቆጠሩ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ተተከሉ፤ የአእላፋት ነፍሳት ጨለማ በራ። በጊዜውም ያለጊዜውም፥ በሰላምና በጦርነት፥ ሲመቻቸውና ሳይመቻቸው የክርስቶስን ወንጌል ለመመስከር ነፍሳቸውን ያስጨከኑትን እኒህን አባቶች የቤተክርስቲያን ታሪክ በክብር ሲዘክራቸው ይኖራል።

የግርጌ ማስታወሻዎች
ምዕራፍ አምስት

[1] የኢትዮጵያ ታሪክ 1848 1966 ፡ ገጽ 166

[2] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 169 ።

[3] ብርሃኑ ደረሰ ፡ ገጽ 26

[4] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 28

[5] ላጵሶ ጌ·ድሌዐ ፡ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም ፡ 1900 1966 ፡ ገጽ 69

[6] Fire on the mountain. P. 122

[7] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 120

[8] Berhanu Deresse. P. 8

[9] የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ···፡ ገጽ 70

[10] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 70

[11] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 71

[12] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 71

[13] ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (ባላቡን ጊታ) ፡ ዝክረ ነገር ፡ ገጽ 526 ።

[14] Markakis John. Ethiopia An Atomy of Traditional Polity. P. 31.

[15] Eide. P. 33

[16] የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848ዓ 1966 ፡ ገጽ 181 ።

13 ·